## እየኖርን ሌሎች እንዲኖሩ እናድርግ!

የአብክመ የኤች.አይ.ቪ/ኤድስ መከ/መቆ/ ሴክሬታሪያት

# በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት መንግስታዊ ተቋማት፣ መ.ያ.ድ፣ ህብረተሰብ አቀፍ ማህበራትና የግል ድርጅቶች ኤድስን በመከላከል ዙሪያ መፈፀም የሚገባቸውን ዘርፈ ብዙ ተግባራት የሚያሳይ ጠቋሚ የሥራ መመሪያ



በአብክመ የኤች.አይ.ቪ/ኤድስ መከ/መቆ/ ሴክሬታሪያት
የተዘጋጀ
መስከረም 1996 ዓ.ም
ባህርዳር

## ማሳሰቢያ

የሥራ ዝርዝሩ ለመነሻነት የሚያገለግል እንጂ በራሱ የመጨረሻ አለመሆኑን ከግምት ውስጥ በማስገባት በፀረ ኤድስ እንቅስቃሴ ተሳታፊ የሆነ ሁሉ አቅምን ባገናዘበ መልኩ የራሱን ፈጠራዊ ተግባር በማከል ዕቅድ ነድፎ መንቀሳቀስ ይገባዋል።

## ዝምታው ይብቃን !

☎ 08-20 63 36

Fax 08-20 68 67

✉ 449



## ማውጫ


| ተ.ቁ | ርዕስ | ገጽ |
|---|---|---|
| 1. | መግቢያ | 4 |
| 1.1 | ዓላማ | |
| 1.2 | ትኩረት የሚሰጣቸው የኅብረተሰብ ክፍሎች | |
| 1.3 | አቅጣጫዎችና ስልቶች | |
| 1.4 | ትኩረት የሚሰጣቸው ተግባራት | |
| 2. | ግብርና | 11 |
| 3. | ትምህርት | 14 |
| 4. | ጤና | 17 |
| 5. | ወጣቶች ፣ባህልና ስፖርት | 21 |
| 6. | ማስታወቂያና ህዝብ ግንኙነት | 25 |
| 7. | ሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ | 28 |
| 8. | ንግድ፣ኢንዱስትሪና ከተማ ልማት | 31 |
| 9. | ፍትህ ፣ ፀጥታና አስተዳደር | 34 |
| 10. | ገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት | 37 |
| 11. | ህዝብ ተሳትፎና አደረጃጀት | 40 |
| 12. | ሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን | 44 |
| 13. | አደጋ መከላከልና ዝግጁነት | 47 |
| 14. | አስተዳደር ጽ/ቤቶች | 50 |
| 15. | ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት | 52 |
| 16. | ሌሎች የመንግስት መስሪያ ቤቶች | 55 |
| 17. | መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች | 57 |
| 18. | ህብረተሰብ አቀፍ ማህበራት | 61 |
| 19. | የሃይማኖት ተቋማት | 64 |

# 1. መግቢያ

በአሁኑ ጊዜ በአለም ደረጃ 42 ሚሊዮን ሰዎች ከኤች.አይ.ቪ ቫይረስ ጋር ይኖራሉ ተብሎ ይገመታል:: ከነዚሁ 28.1 ሚሊዮን በአፍሪካ በተለይም ከስሃራ በታች ባሉ አገሮች ይገኛሉ:: በአገራችን ኢትዮጵያም 2.2 ሚሊዮን ዜጎች ከቫይረሱ ጋር እንደሚኖሩ ይገመታል:: ከነዚህ ውስጥ 200000 ያህሉ ሕፃናት ናቸው::

በክልላችንም በ2001 እ.ኤ.አ በደም ለጋሾች ላይ በተደረገ ምርመራ የበሽታው የስርጭት መጠን 8.1 ሲሆን የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር በኦክቶበር 2002 እ.ኤ.አ ባወጣው እትሙ በ2001 በክልላችን በተለያዩ አካባቢዎች በነፍሰ ጡሮች ላይ በተደረገ የደም ምርመራ በጎንደር ጤና ጣቢያ 15.1 በመቶ፣ በእስቴ ጤና ጣቢያ 10.7 በመቶ እንዲሁም በባህርዳር ጤና ጣቢያ 23.4 በመቶ ያህል ቫይረሱ እንደተገኘባቸው ይፋ አድርጓል::

ከላይ መረጃው እንደሚያሳየው ቫይረሱ በክልላችን በአደገኛ ሁኔታ እየተሰራጨ መሆኑንና በተለይም ባህርዳር በሀገሪቱ ምርመራ ከተካሄደባቸው ከተሞች ከፍተኛውንና የመጀመሪያውን ደረጃ መያዟን ያመላክታል::

ሀገራችን በአሁኑ ወቅት 67 ሚሊዮን ሕዝብ እንዳላት የሚገመት ሲሆን ከዚህ ውስጥ ከ15 እስከ 49 ዕድሜ ክልል የሚገኘውና አምራች የሆነው ኃይል የሚባለው ክፍል ወደ 29.7 ሚሊዮን የሚጠጋ ነው::

በተለይም በኤች.አይ.ቪ/ኤድስ በሽታ የሚያዘውና ማህበራዊ ግዴታውን ሳይፈፅም ቶሎ የሚሞተው ይህ ክፍል ነው:: ይህ የዕድሜ ክልል በኢኮኖሚ ዘርፍ ከፍተኛ አምራች ኃይል ያሉበት መሆኑን ስንመለከት ወረርሽኙ በምርታማነት ላይ የሚያስከትለው አሉታዊ ተፅእኖ ቀላል አለመሆኑን እንገነዘባለን:: በበሽታው ምክንያት የሥራ ሰዓት ይባክናል:: መደበኛ ሥራን ለማከናወን የሚያስፈልገው አቅምም እየቀነሰ ከመሄዱም በላይ የአምራቹ ኃይል በበሽታው መጠቃት አመታዊ የዕድገት ደረጃችንን ሊቀንሰው ይችላል:: ይህ ሁሉ ተደምሮ በልማታችን ላይ አሉታዊ ተፅፅኖ ያሳድራል::



በሽታውን ለመከላከልና ለመቆጣጠር በርካታ ሥራዎች የተከናወኑ ሲሆን ከእነዚህም ውስጥ የተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎችን ያካተተ የኤች.አይ.ቪ/ኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ ም/ቤቶችን በየደረጃው እንዲቋቋሙ ከመደረጉም በላይ በአገር አቀፍ ደረጃ ነሐሴ1/1990 ዓ.ም የኤድስ ፖሊሲ ወጥቶ ተግባራዊ በመደረግ ላይ ነው:: በፖሊሲው ገጽ 7 ላይ በግልጽ እንደተመለከተው ሁሉም መንግሰታዊ መ/ቤቶች ዘርፎች፣ የብዙሃን ማህበራት፣ የኃይማኖት ተቋማት፣ የሙያ ማህበራት እንዲሁም አጠቃላይ ህብረተሰቡ የኤድስ ወረርሽኝን ለመከላከል ትኩረት ሰጥተው ቀጥተኛ ተሳትፎ ማድረግ እንዳለባቸው ያስገነዝባል::

የአገር አቀፍ ኤች.አይ.ቪ/ኤድስ መከ/መቆ/ም/ቤት መቋቋምን ተከትሎ በክልላችንም ከህዳር 1993 ዓ.ም ጀምሮ የክልሉ የኤች.አይ.ቪ/ኤድስ መከ/መቆ/ም/ቤትና ሴክሬታሪያት ተቋቁሟል:: በተጨማሪም ከክልል እስከ ቀበሌ የተዘረጋ አደረጃጀት ተፈጥሮ የተለያዩ የመንግስት ፣መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችና ህብረተሰቡ በሽታውን በመከላከል ዙሪያ የበኩላቸውን ጥረት በማድረግ ላይ ይገኛሉ::

ተልዕኮው ግልጽና የማያሻማ ይሁን እንጅ ይህ ቅንጅታዊ ስትራቴጅ በአንፃራዊነት ከአሁን ቀደም ካደረግናቸው እንቅስቃሴዎች ለየት ያለ በመሆኑ ማን ምን ይስራ የሚለውን በተመለከተ በሁሉም አካላት በቂ ግንዛቤ ባለመኖሩ ምክንያት ዕቅድን መሠረት ያደረጉ ተግባራትን በበቂ ሁኔታ ማከናወን አልተቻለም::

በዚህ መሠረት ለችግሩ መፍትሔ በማፈላለግ ረገድ ብቃት ያለው ሙያዊ ዕገዛ ለማድረግ፣ ምቹ ሁኔታን ለመፍጠርና የሥራ ድግግሞሽን ለማስቀረት እንዲሁም የመፈፀም ብቃትን ለማጎልበት እንዲቻል የክልሉ የኤች.አይ.ቪ/ኤድስ መከ/መቆ/ሴክሬታሪያት ይህንን የመነሻ ፅሑፍ አዘጋጅቶ አቅርቧል:: ዝርዝር ተግባራቱም ሲዘጋጁ በቅርቡ የተደረገውን የመንግስት መ/ቤቶች አደረጃጀት ግምት ውስጥ ለማስገባት ተሞክሯል:: በክልላችን የሚገኙ የመንግስት መስሪያ ቤቶችን በሙሉ በዝርዝር ለማየት ቢሞከር ድግግሞሽ ሊያስከትል ስለሚችልና ስፋትም ስለሚኖረው በተቻለ መጠን ከመስሪያ ቤቱ ስፋትና የሰው ኃይል እንዲሁም ከሌላው የህብረተሰብ ክፍል ጋር የሚኖረውን ግንኙነት ግምት ውስጥ በማስገባት የተወሰኑትን በፅሑፉ ውስጥ ለማሳየት ተሞክሯል:: አንዳንድ መስሪያ ቤቶችንም ለዚህ ተግባር ሲባል ብቻ ተመሳሳይ የሥራ ባህሪይ የሚኖራቸውን ከሌሎች ጋር ለማካተት ተሞክሯል:: ለምሳሌ አስተዳደርና ፀጥታ ጉዳዮች ቢሮን

ከፍትህ ቢሮ ጋር በማጣመር "ፍትህ፣ ፀጥታና አስተዳደር" በሚል ለማሳየት ተሞክሯል:: ይህም የሆነበት ምክንያት ሁሉቱም መስሪያ ቤቶች ኤች.አይ.ቪ/ኤድስን ለመከላከል የሚኖራቸው ድርሻ ተመሳሳይ በመሆኑና ድግግሞሽን ለማስቀረት ሲባል ነው:: በመሆኑም በፅሁፍ ውስጥ ያልተጠቀሱ መስሪያ ቤቶች ከተዘረዘሩት መስሪያ ቤቶች ውስጥ ሊካተቱበት የሚችሉትን በመለየት /ለምሳሌ ትራንስፖርትና መገናኛ በንግድ፣ ኢንዱስትሪና ከተማ ልማት ቢሮ ውስጥ ስለሚገኝ/ ወይም በፅሁፉ ላይ ሌሎች መ/ቤቶች የሚለውን እንደመነሻ በመውሰድ እንደመስሪያ ቤቱ የሥራ ባህሪይ ያልተጠቀሱ ሌሎች ተጨማሪ ተግባራትን አክሎ በማቀድ መንቀሳቀስ የሚችሉ መሆኑን ለመግለጽ እንወዳለን:: ስለዚህ ኤች.አይ.ቪ/ኤድስን በመከላከል ረገድ ሁሉም የኀብረተሰብ ክፍል የድርሻውን እንዲወጣ ለመነሻነት እንዲያገለግል ይህ የሥራ መመሪያ ተዘጋጅቷል::

## 1.1 ዓላማ

የዚህ ፅሑፍ ዋና ዓላማ በክልላችን የሚገኙ መንግስታዊ ፣ መያድና ህብረተሰብ አቀፍ ማህበራት ኤች.አይ.ቪ/ኤድስን ለመከላከልና ለመቆጣጠ ር በሚደረገው ጥረት ምን መስራት እንዳለባቸው ለማሳየት ሲሆን የሚመለከተው ሁሉ ከመደበኛ ሥራው ጋር የኤች.አይ.ቪ/ኤድስን ሥራ በማዋሃድ እንዲንቀሳቀሱ ለማስቻልና በዚሁ መሠረት

- ኤች.አይ.ቪ/ኤድስ በሠራተኞችና በቤተሰቦቻቸው ላይ የሚያደርሰውን ጥቃት ለመከላከልና ለመግታት፣
- ኤች.አይ.ቪ/ኤድስ በሀገሪቱ ዕድገት ላይ የሚያደርሰውን ተፅእኖ ለመቀነስና ሠራተኛውና መላው ኀብረተብ በዚሁ ረገድ የበኩሉን አስተዋጽኦ እንዲያደረግ ለማስቻል ነው::

## 1.2 ትኩረት ሊሰጣቸው የሚገባ የህብረተሰብ ክፍሎች

1. ወጣቶች፣
2. ወላጅ አልባ ሕፃናቶችና ልጆች ፣
3. ሴቶች፣
4. የአእምሮና የአካል ጉዳተኞች፣
5. ሠራተኞች / ላብ አደሮች፣
6. አርሶ አደሮች፣



7. ከቫይረሱ ጋር የሚኖሩ ሰዎች እና
8. ቤተሰብ ናቸው ::

## 1.3. አቅጣጫዎች / ስልቶች

- በመስሪያ ቤቱ ወይም በተቋሙ ውስጥ ከስራው ጋር ቀረቤታ ያለውን ባለሙያ የኤች.አይ.ቪ/ኤድስን እንቅስቃሴ እንዲያስተባብር መሰየምና የሥራ ድርሻውን በሥራ ዝርዝሩ ውስጥ እንዲካተት ማድረግ፣
- ከሠራተኞች ወይም ከማህበረሰቡ የስራ ባህሪይና ለቫይረሱ የመጋለጥ አደጋ ጋር የተጣጣመ የመከላከል ኘሮግራም መከተል፣
- በየመ/ቤቱ ወይም በየተቋሙ አመታዊ ዕቅድ ውስጥ ኤች.አይ.ቪ/ኤድስን የመከላከል ተግባራት እንዲካተቱና እንዲፈፀሙ ማድረግ፣
- አብዛኛው ሠራተኛና ማህበረሰቡ ስለኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ያለውን ግንዛቤና ባህርይ ለማሻሻል የተለያዩ የማስተማሪያና የቅሰቀሳ መድረኮች እንዲዘጋጁ ሁኔታዎችን ማመቻቸት፣
- በመከላከሉ ሥራ ላይ ኃላፊዎችና የሥራ አመራር አካላት የነቃ ተሳትፎ እንዲኖራቸው ማበረታታትና ቅንጅታዊ አመራር የጎለበተ እንዲሆን ማስቻል፣
- ሀብትን ውጤታማ በሆነና ወጪን በሚቀንስ መንገድ ሥራ ላይ ማዋል፣

## 1.4. ኤች.አይ.ቪ/ኤድስን ለመከላከልና ለመቆጣጠር ትኩረት የሚሠጣቸው ተግባራት/ እርምጃዎች

1. የመረጃ ትምህርትና ሥርፀት / የባህሪ ለውጥ ስርፀት /IEC/ BCC/ ኘሮግራም ፣
2. በፈቃደኝነት ላይ የተመሠረተ የኤች.አይ.ቪ. ምርመራና የምክር አገልግሎት /VCT/
3. የአባለዘር በሽታዎች መከላከልና ሕክምና /STI/
4. የኮንዶም ሥርጭትና አጠቃቀም፣
5. በሕክምና ተቋማት ስለኤች.አይ.ቪ. የሚደረጉ አጠቃላይ ጥንቃቄዎችን ማጠናከር፣
6. ከኤድስ ቫይረስ ነፃ የሆነ የደም አቅርቦት፣
7. ከእናቶች ወደ ህፃናት ኤች.አይ.ቪ. እንዳይተላለፍ መከላከል፣
8. ለኤድስ ሕሙማን የቤት ውስጥ እንክብካቤ ማድረግ፣

9. ለኤድስ ሕሙማን በጤና ተቋማት እንክብካቤ ማድረግ፣
10. መረጃ ማሰባሰብ የምርምርና ሥርፀት ሥራ ማከናወን፣

**ኤድስ የኔ ችግር ነው !**

**ያንተም፣ ያንችም ችግር ነው !**

**የኛም ችግር ነው !**



# 1. ግብርና

በአብዛኛው የክልላችን ህዝብ የሚኖረው በገጠር ሲሆን የተሰማራው በግብርና ሥራ ላይ ነው:: የከተማው ህዝብ ኑሮ የተመሰረተው በዚሁ በገጠር በሚኖረው ህዝብ ላይ ነው:: በመሆኑም የገጠሩን ህዝብ ጤንነት መጠበቅ አጠያያቂ አይሆንም::

በቅርቡ የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ባወጣው ትንበያ መሠረት በከተማ ከ100 /አንድ መቶ/ ለአቅመ አዳም የደረሱ ሰዎች አስራ ሦስቱ ቫይረሱ እንደሚገኝባቸው እና በገጠር ደግሞ 5% እንደሚደርስ ይጠቁማል::

እንደ ከተማው ሁሉ በገጠሩም ወላጅ አልባ ህፃናትና ጧሪ አልባ አረጋውያን ቁጥር መበራከት ከኤድስ ጋር ተያያዥነት እንዳለው መገመት አያዳግትም:: በመሆኑም 85% የሚሆነው የአገራችን የህብረተሰብ ክፍል የሚያቅፈውን የአርሶአደር ህይወት ከመለወጥ ጐን ለጐን የኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ስርጭትን ለመቆጣጠርና ለመከላከል እንዲቻል በዚህ ዘርፍ የሚከተሉትን ተግባራት ማከናወን ይጠበቃል::

## ተግባራት

- በዘርፉ ፀረ-ኤድስ እንቅስቃሴዎችን ማቀድና ተግባራዊ የሚሆንበትን መንገድ ማመቻቸት፣
- በየደረጃው በሚገኙ ጽ/ቤቶች የፀረ ኤድስ እንቅስቃሴን የሚከታተል ባለሙያ /Focal person/ መሰየም፣

- በዘርፉ የሚገኙ ሠራተኞች ራሳቸውንና ቤተሰቦቻቸውን ከበሽታው እንዲጠብቁ የተጠናከረ የፀረ-ኤድስ ሥራ መስራት፣
- በገጠሩ አካባቢ የኤች.አይ.ቪ/ኤድስ መስፋፋት ምክንያት የሆኑትን ጐጂ፣ ባህላዊና ልማዳዊ ድርጊቶች /ያለ ዕድሜ ጋብቻ፣ ግርዛት፣ የግዳጅ ጋብቻ፣ ጠለፋ፣ ወዘተ…/ የመሳሰሉት እንዲወገዱ የሚያስችሉ ስልቶችን በመዘርጋት ጥረት ማድረግ፣
- በዘርፉ የሚገኙ ሠራተኞችና አርሶአደሮች በፈቃደኝነት ላይ የተመሠረተ የኤች.አይ.ቪ ደም ምርመራ እንዲያደርጉ ማበረታታትና ሁኔታዎችን ማመቻቸት ፣
- አርሶአደሮች በማህበሮቻቸውና በግላቸው ተደራጅተው ስለኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ያላቸውን ግንዛቤ እንዲያዳብሩ ማገዝ፣
- በገጠር የሚገኙ የልማት ጣቢያ ሠራተኞችን በመጠቀም ለአርሶ አደሮች በሽታውን በተመለከተ የተጠናከረ ትምህርት መስጠት፣
- አርሶ አደሮች እንደየእምነቶቻቸውና ሀይማኖቶቻቸው መልካም ስነ ምግባር እንዲያዳብሩ በሀይማኖት አባቶች በኩል የሚሰጠውን ምክርና ትምህርት ማጠናከር፣
- ከአርሶ አደሩ መካከል ማንበብና መፃፍ የሚችሉትን በመመልመል አጭር ስልጠና በመስጠት እርስ በእርስ የሚማማሩበትን ሁኔታ መፍጠር፣
- በገጠሩ አካባቢ ለበሽታው ይበልጥ ሊጋለጡ የሚችሉትን ወጣት አርሶ አደሮች፣ ከተማ ቀመስ አርሶ አደሮችና የመሳሰሉት ላይ ትኩረት በማድረግ ተከታታይነት ያለው ትምህርት መስጠት፣



- ከቫይረሱ ጋር ለሚኖሩ ፣ ለኤድስ ህሙማን እና በኤድስ ምክንያት ወላጆቻቸውን ላጡ ልጆች አርሶ አደሩን ባሳተፈ መልኩ የገቢ ማሰባሰቢያ ኘሮግራሞችን በማዘጋጀት ድጋፍና እንክብካቤ ማድረግ፣
- በፀረ- ኤድስ እንቅሰቃሴ ዙሪያ ኘሮጀክቶችን መቅረጽና ድጋፍ በማፈላለግ ተግባራዊ ማድረግ፣
- የግብርና ባለሙያዎች የኘሮጀክት ሀሳቦችን በማመንጨት በየደረጃው ለሚገኙ የፀረ- ኤድስ ኮሚቴዎች ሙያዊ ድጋፍ ማድረግ፣
- የመረጃ ፣ትምህርትና ስርፀት የባህሪ ለውጥ ስርፀት ( IEC/BCC ) ማቴሪያሎችን በማዘጋጀት ወይም በማሰባሰብ ለአርሶ አደሩ እንዲዳረሱ ማድረግ፣
- ኤች.አይ.ቪ/ኤድስን በሚመለከት የሚወጡ ፖሊሲዎች ፣ መርሀ ግብሮችን ፣ መመሪያዎች ፣ አዋጆችና ደንቦችን ለህብረተሰሱ ማስተዋወቅ፣
- የተሻለ የፀረ ኤድስ እንቅስቃሴ ካላቸው ክፍሎች ጋር የልምድ ልውውጥ ማድረግ፣
- በፀረ-ኤድስ እንቅስቃሴ ዙሪያ ከተሰማሩ አካላት ጋር በቅንጅት መስራት፣
- የኤች.አይ.ቪ/ኤድስን ስርጭት፣ ገጽታና የህብረተሰቡን የባህርይ ለውጥ በሚመለከት የቅኝትና ጥናታዊ ሥራ መስራት፣
- በዘርፉ በተደረገው የፀረ-ኤድስ አንቅሰቃሴ የተገኘውን ለውጥ መገምገም፣
- ኤች.አይ.ቪ/ኤድስ በዘርፉ እያደረሰ ያለውን ተፅእኖ በመረጃ አስደግፎ መገምገምና ማሳወቅ፣
- የተከናወኑ የፀረ ኤድስ ተግባራትን በወቅቱ ለሚመለከተው አካል ሪፖርት ማድረግ::

# 3.ትምህርት

እንደሚታወቀው በኤች.አይ.ቪ/ኤድስ በይበልጥ እየተጠቃ ያለው የህብረተሰብ ክፍል በመማርና ማስተማር ላይ የተሰማራው አምራች ዜጋ ስለመሆኑ የተለያዩ መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡ በዚህም መሠረት በሽታው በአገራችን ኢኮኖሚያዊ ፣ማህበራዊና ስነ ልቦናዊ ቀውሶችን እያስከተለ ይገኛል፡፡ ስለዚህ በዚህ ዘርፍ የተጠናከረ ሥራ መስራት ይጠበቅብናል፡፡

## ተግባራት

- በዘርፉ ፀረ ኤድስ እንቅሰቃሴዎችን ማቀድና ከመደበኛው ሥራ ጋር በማጣመር ተግባራዊ የሚሆንበትን መንገድ ማመቻቸት፣
- በዘርፉ በየደረጃው በሚገኙ ጽ/ቤቶች የፀረ-ኤድስ እንቅስቃሴን የሚያስተባብር ባለሙያ /Focal Person/ መሰየምና ከሚመለከታቸው ጋር የተጠናከረ የሥራ ግንኙነት መፍጠር፣
- በዘርፉ የሚገኙ መምህራን፣ ሰራተኞችና ተማሪዎች ራሳቸውንና ቤተሰቦቻቸውን ከበሽታው እንዲጠብቁ የተጠናከረ የፀረ-ኤድስ ሥራ ማከናወን፣



- በአንደኛና በሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች እንደየአካባቢው ሁኔታ ተስማሚ የሆነ የኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ትምህርት በስርዓተ ትምህርቱ ውስጥ እንዲካተት በማድረግ ማስተማር፣
- በክልሉ በሚገኙ ት/ቤቶች የፀረ ኤድስ ክበባት እንዲቋቋሙ ማድረግና ማጠናከር፣
- የት/ቤት ተማሪዎች፣ መምህራንና ወላጆቻቸው በበሽታው ዙሪያ መወያየት የሚችሉበትን የጋራ መድረክ መፍጠር፣
- ኤች.አይ.ቪ/ኤድስን በመከላከል ዙሪያ የሴት ተማሪዎችን ተሳትፎ ማሳደግ
- በት/ቤቶች በየደረጃው የፆታ ትምህርት የሚሰጥበትን ሁኔታ ማመቻቸት
- ኤች.አይ.ቪ/ኤድስ በተመለከተ ለመምህራን ሠራተኞችና ተማሪዎች የተለያዩ ስልጠናዎችን መስጠትና አፈፃፀሙን መከታተል፣
- መምህራንና ተማሪዎች በአካባቢያቸው የሚገኙ ጐጂ ባህላዊና ልማዳዊ ድርጊቶች እንዲወገዱ የበኩላቸውን ጥረት እንዲያደርጉ ማገዝ፣
- በፀረ-ኤድስ እንቅስቃሴ ዙሪያ ፕሮጀክቶችን በመቅርጽ ለሚመለከታቸው አካላት ማቅረብና ተግባራዊ ማድረግ ፣
- ከቫይረሱ ጋር ለሚኖሩ ፣ ለኤድስ ህሙማንና በኤድስ ምክንያት ወላጆቻቸውን ላጡ ልጆች እንክብካቤና ድጋፍ ለማድረግ የተለያዩ የገቢ ማስገኛ ፕሮግራሞችን ማዘጋጀት፤ ወላጅ አልባ ተማሪዎች ትምህርታቸውን እንዳያቋርጡ ጥረት ማድረግ፣
- የመረጃ ትምህርትና ስርፀት /የባህሪ ለውጥ ስርፀት ( IEC/BCC ) ማቴሪያሎችን በማዘጋጀት ወይም በማሰባሰብ ለማህበረሰቡ ማሰራጨት፣
- ኤች.አይ.ቪ/ኤድስን በሚመለከት የሚወጡ ፖሊሲዎች ፣ መርህ ግብሮች፣ መመሪያዎች ፣ አዋጆችና ደንቦችን ለማህበረሰቡ ማስተዋወቅ፣

- የተሻለ የፀረ-ኤድስ እንቅስቃሴ ካላቸው ክፍሎች ጋር የልምድ ልውውጥ ማድረግ፣
- በፀረ-ኤድስ እንቅስቃሴ ዙሪያ ከተሰማሩ አካላት ጋር በቅንጅት መስራት፣
- በዘርፉ የሚገኙ መምህራን ፣ ሠራተኞችና ተማሪዎች በፈቃደኝነት ላይ የተመሰረተ የኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ደም ምርመራ እንዲያደርጉ ማበረታታትና ሁኔታዎችን ማመቻቸት፣
- የኤች.አይ.ቪ/ኤድስን ስርጭት ፣ ገጽታ፣ ተፅእኖና የህብረተሰቡን የባህርይ ለውጥ በሚመለከት ከሚመለከታቸው ጋር በመተባበር የቅኝትና ጥናታዊ ሥራ መስራት፣ግኝቱንም ማሰራጨት፣
- በዘርፉ በተደረገው የፀረ-ኤድስ እንቅስቃሴ የተገኘውን ለውጥ መገምገም፣
- የተከናወኑ የፀረ-ኤድስ ተግባራትን በወቅቱ ለሚመለከተው አካል ሪፖርት ማድረግ::

***የለውጥ ኃይል ከሆነው ወጣት ጋር***



# ኤች.አይ.ቪ/ኤድስን እንከላከል !

## 4. ጤና

በአገራችን ያለው የጤና አገልግሎት ሽፋን ዝቅተኛ ከመሆኑም በላይ ተላላፊ በሽታዎች በከፍተኛ ደረጃ ተስፋፍተው ስለሚገኙ በህዝቡ ላይ የሚያደርሱት የህመም ስቃይና ሞት ቀላል ግምት የሚሰጠው አይደለም:: በዚህ ሁኔታ ላይ ከአለፉት ሁለት አስርት አመታት ወዲህ ተከስቶ በከፍተኛ ፍጥነት እየተሰራጨ ያለው የኤድስ በሽታ ተጨምሮበት የጤና ችግሩን ይበልጥ አባብሶታል:: በመሆኑም ኤች.አይ.ቪ/ ኤድስን ለመከላከል በሚደረገው የጋራ ጥረት በጤናው ዘርፍ ያለው ሚና በዋነኛነት የሚጠቀስ ሲሆን በተለይም ትኩረት ከሚሰጣቸው እርምጃዎች /ፕሮግራሞች/ ውስጥ በፈቃደኝነት ላይ የተመሠረተ የኤች.አይ.ቪ/ ኤድስ የደም ምርመራና የምክር አገልግሎት፣ የአባለ ዘር በሽታዎች ቁጥጥርና ህክምና፣ የኮንዶም ስርጭትና አጠቃቀም ፣ ደህንነቱ የተጠበቀ የደም አቅርቦትና ኤች.አይ.ቪ ከእናቶች ወደ ሕፃናት እንዳይተላለፍ በመከላከል ረገድ ጉልህ አስተዋጽኦ አለው:: በዚህ ዘርፍ ኤች.አይ.ቪ/ኤድስን ለመከላከልና ለመቆጣጠር የሚከተሉትን ተግባራት ማከናወን ይጠበቃል::

**ተግባራት**

- በዘርፉ ፀረ-ኤድስ እንቅስቃሴዎችን ማቀድና ተግባራዊ የሚሆንበትን መንገድ ማመቻቸት፣
- በዘርፉ በየደረጃው በሚገኙ ጽ/ቤቶች የፀረ ኤድስ እንቅሰቃሴ የሚከታተል ባለሙያ /Focal person/ መሰየም፣
- በዘርፉ የሚገኙ ሰራተኞች ራሳቸውንና ቤተሰቦቻቸውን ከበሽታው እንዲጠብቁ የተጠናከረ የፀረ ኤድስ ስራ መስራት፣
- ለኤች.አይ.ቪ/ኤድስ መስፋፋት ምክንያት የሆኑትን ጎጂ ባህላዊና ልማዳዊ ድርጊቶች እንዲወገዱ ጥረት ማድረግ፣
- በዘርፉ የሚገኙ ሰራተኞችና ከስራው ጋር ተያያዥነት ያላቸው የህብረተሰብ ክፍሎች በፈቃደኝነት ላይ የተመሰረተ የኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ደም ምርመራ እንዲያደርጉ ማበረታታትና ሁኔታዎችን ማመቻቸት፣
- ለህብረተሰቡ ለደም ምርመራ አስፈላጊ የሆኑ ቁሳቁሶች በበቂ ሁኔታ እንዲሟሉ ጥረት ማድረግ፣
- ተጨማሪ የምርመራ ጣቢያዎችን ማስፋፋትና የተጠናከረ የጥራት ቁጥጥር ሥራ መስራት፣
- በጤና ተቋማት ከኤች.አይ.ቪ ነፃ የሆነ የደም አቅርቦትን ማረጋገጥ፣
- በጤና ተቋማት ለኤድስ ህሙማን ተገቢውን ህክምናና እንክብካቤ ማድረግ፣
- በህክምና ተቋማት የኤች.አይ.ቪ/ኤድስ መተላለፊያ መንገዶችን ለመዝጋት ሁለንተናዊ ጥንቃቄ ማድረግ፣
- በጤና ተቋማት በቂ የሆነ የኮንዶም አቅርቦትና ስርጭት እንዲኖር ማድረግና አፈፃፀሙን መከታተል፣
- የአባለዘር በሽታዎችን ህክምናና አገልግሎት ስርዓትን ማጠናከር ፣

የአብክመ የኤች.አይ.ቪ/ኤድስ መከ/መቆ/ ሴክሬታሪያት

- ለበሽታው ፈውስ የሚያስገኙ መድሃኒቶችን በማፈላለግ ረገድ፣ ባህላዊ ሙከራዎችን ከዘመናዊው ጋር እንዲቀናጁ ሥልት በመቀየስ ሥራ ላይ ማዋል፣
- ኤች.አይ.ቪ/ኤድስን በመከላከልና በመቆጣጠር ዙሪያ ለተሰማሩ አካላት አስፈላጊውን ሙያዊ እገዛ ማድረግና ተቀናጅቶ መስራት፣
- በክልሉ በሚገኙ በመንግስት፣ በግልና በመያድ የጤና ድርጅቶች የፈቃደኝነት የኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ምርመራና የምክር አገልግሎት እንዲጀመር፣ እንዲጠናከርና እንዲስፋፉ ማድረግ፣
- በመንግስት፣ በግልና በመያድ የጤና ድርጅቶች የሚሰጠውን የኤች.አይ.ቪ ምርመራና የምክር አገልግሎት ጥራት ማስጠበቅ፣ መከታተል፣መቆጣጠርና የሚላኩ ሪፖርቶችን ለቀጣይ ሥራዎች ግብዓት እንዲሆኑ ማድረግ፣
- በኤች.አይ.ቪ/ኤድስ መከ/መቆ/የሚቀርቡ የግል፣ መያድና ሌሎች መ/ቤቶች የጤናው ዘርፍ ተግባራት የሚመለከቱ ኘሮፖዛሎችን መገምገም፣ ክንዉናቸውን መከታተልና የሚያስገኙትን ውጤት በመመዘን በሰፊው ሥራ ላይ ማዋል፣
- በፀረ ኤድስ እንቅሰቃሴ ዙሪያ ኘሮጀክቶችን በመቅረጽ ከሚመለከታቸው አካላት ድጋፍ በማፈላለግ ተግባራዊ ማድረግ፣
- የመረጃ፣ ትምህርትና ስርፀት/የባህሪ ለውጥ ሥርፀት ( IEC/BCC ) ማቴሪያሎች በማዘጋጀት ወይም በማሰባሰብ ለህብረተሰቡ እንደሰራጩ ማድረግ፣
- የዕድሜ ማራዘሚያና ከእናት ወደ ልጅ ቫይረሱ እንዳይተላለፍ የሚረዱ መድሃኒቶችን በክልሉ ጥቅም ላይ የሚውሉበትን ሁኔታ ማመቻቸት ፣

- ከቫይረሱ ጋር ለሚኖሩ፣ ለኤድስ ህሙማንና በኤድስ ምክንያት ወላጆቻቸውን ላጡ ሕፃናት እንክብካቤና ድጋፍ ለማድረግ የተለያዩ የገቢ ማስገኛ ኘሮግራሞችን ማዘጋጀት፣
- ኤች.አይ.ቪ/ኤድስን በሚመለከት ለሚወጡ ፖሊሲዎች፣ መመያዎችና መርሃ ግብሮች ጠቃሚ የፖሊሲ ሀሳቦችን ማመንጨት፣
- ኤች.አይ.ቪ/ኤድስን በሚመለከት የሚወጡ ፖሊሲዎች፣ መርሀ ግብሮች፣ መመሪያዎች፣ አዋጆችና ደንቦችን ለህብረተሰቡ ማስተዋወቅ፣
- የተሻለ የፀረ ኤድስ እንቅስቃሴ ካላቸው ክፍሎች ጋር የልምድ ልውውጥ ማድረግ፣
- የኤች.አይ.ቪ/ኤድስን ስርጭት፣ ገፅታ፣ ማህበራዊ ተፅእኖውንና የሕብረተሰቡን የባህሪይ ለውጥ በሚመለከት የቅኝት ጥናትና የምርምር ሥራ መሥራት፣ውጤቱንም ማሠራጨት፣
- ኤች.አይ.ቪ/ኤድስን በተመለከተ የተለያዩ ስልጠናዎች መስጠትና ተግባራዊነቱን መከታተል፣
- በዘርፉ በሚደረገው የፀረ ኤድስ እንቅስቃሴ የሚገኘውን ለውጥ መገምገም፣
- የተከናወኑ የፀረ-ኤድስ ተግባራትን በወቅቱ ለሚመለከተው አካል ሪፖርት ማድረግ፡፡

የአብክመ የኤች.አይ.ቪ/ኤድስ መከ/መቆ/ ሴክሬታሪያት

**ጋብቻ ከመፈፀምዎ በፊት የኤች.አይ.ቪ ደም ምርመራ ማድረግን አይዘንጉ !**

## 5. ወጣቶች፣ ባህልና ስፖርት

ወጣቶች በእድሜአቸው አፍላነት ምክንያት ግብታዊ በሆነ ስሜት የሁኔታዎችን ጥቅምና ጉዳት ካለማገናዘብ የተነሳ ሕይወታቸውን አደጋ ላይ ሊጥሉ የሚችሉ ጥንቃቄ የጎደላቸው ድርጊቶችን ስለሚፈፅሙ ለተለያዩ አደጋዎች የተጋለጡ ናቸው፡፡

የተለያዩ ጥናቶች እንደሚጠቁሙት ወጣቶች ለአደንዛዥ ዕፅ ተገዥ በመሆን፣ አልባሌ ቦታዎች በመዋል፣ ላልተፈለገ እርግዝና፣ በወሲብ ምክንያት ለሚተላለፉ በሽታዎች፣ ለህገ ወጥ ውርጃ፣ ለወሲብ ጥቃት፣ ለተለያዩ ጎጂ ልምዶችና ለወንጀል የተጋለጡ ናቸው፡፡ በአጠቃላይ ወጣቶች በጤናቸውና በሕይወታቸው ላይ አደጋ ሊያመጡ የሚችሉ ነገሮችን ለመፈፀም ይገፋፋሉ፡፡

ስለዚህ ወጣቱን ከእነዚህ አደጋዎች በተለይም ከኤች.አይ.ቪ/ኤድስ መጠበቅ አስፈላጊ በመሆኑ ይህ ዘርፍ የሚከተሉትን ተግባራት ሊያከናውን ይገባል::

## ተግባራት

- በዘርፉ ፀረ ኤድስ እንቅስቃሴዎችን ማቀድና ከመደበኛ ሥራው ጋር በማጣመር ተግባራዊ የሚሆንበትን መንገድ ማመቻቸት፣
- በዘርፉ በየደረጃው በሚገኙ ጽ/ቤቶች የፀረ ኤድስ እንቅስቃሴን የሚያስተባብር ባለሙያ /Focal Person/ መመደብ
- ወጣቱ የሕብረተሰብ ክፍል ትርፍ ጊዜውን ሊያሳልፍባቸው የሚችልበትን የተለያዩ የባህልና የስፖርት ማዘውተሪያ ማዕከሎችን ማስፋፋት፣
- ታዋቂና ተወዳጅ የሆኑ ስፖርተኞችን በመጠቀም ለሕብረተሰቡ ሰፊ የሆነ የፀረ ኤድስ እንቅስቃሴ እንዲያደርጉ ሁኔታዎችን ማመቻቸት፣
- በተለያዩ የስፖርት ውድድሮችና ማዘውተሪያ ስፍራዎች የተጠናከረ የፀረ ኤድስ ቅስቀሳ ማካሄድ፣
- ለኤች.አይ.ቪ/ኤድስ መስፋፋት ምክንያት የሆኑትን ጎጂ ባህላዊና ልማዳዊ ድርጊቶች በመለየት እንዲወገዱ ጥረት ማድረግ፣

- በበጎ ፈቃደኝነት ላይ የተመሰረተ የወጣቶችና የተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች የፀረ ኤድስ ክበባት ማቋቋምና ማጠናከር፣
- ኤድስን አስመልክቶ ለህብረተሰቡ የሚቀርቡ ድራማዎች፣ ስነ ፅሁፎች፣ ሙዚቃዎች ወዘተ.... ኪነ ጥበባዊና ትምህርታዊ ይዘታቸውን መከታተልና መገምገም፣

የአብክመ የኤች.አይ.ቪ/ኤድስ መከ/መቆ/ ሴክሬታሪያት

- ወጣቱን ለስነ ምግባር ብልሹነት የሚዳርጉ ሁኔታዎችን መከታተልና በማስተማር ማስወገድ፣
- ወጣቶች ከሥራ ጠባቂነት እንዲላቀቁ የተለያዩ ስልቶችን መቀየስና ለተግባራዊነቱም ከስነልቦናዊ ዝግጅት ጀምሮ የክህሎት ሥልጠና መስጠት ሥራ ፈጣሪ እንዲሆኑ ማስቻል፣
- በአማተር ደረጃ በፀረ ኤድስ ዙሪያ የሚካሄዱ የኪነ ጥበብ ሥራዎችን ማበረታታና አስፈላጊውን ድጋፍ ማድረግ፣
- ኤች.አይ.ቪ/ኤድስን በሚመለከት ስዕል፣ ቅርፃቅርፅና አሻንጉሊቶችን በመጠቀም የተለያዩ ትምህርታዊ መልዕክቶችን ማስተላለፍ፣
- በዘርፉ የሚገኙ ሰራተኞችና ከስራው ጋር ተያያዥነት ያላቸው የሕብረተሰብ ክፍሎች በፈቃደኝነት ላይ የተመሰረተ የኤች አይ.ቪ.ደም ምርመራ እንዲያደርጉ ማበረታታትና ሁኔታዎችን ማመቻቸት፣
- ኤች.አይ.ቪ/ኤድስን በሚመለከት የተለያዩ ስልጠናዎችን መስጠት፣ ማስተባበርና ተግባራዊነቱን መከታተል፣
- ከቫይረሱ ጋር ለሚኖሩ ወገኖች፣ ለኤድስ ህሙማንና በኤድስ ምክንያት ወላጆቻቸውን ላጡ ልጆች የተለያዩ የገቢ ማሰባሰቢያ ኘሮግራሞችን በማዘጋጀት ድጋፍና እንክብካቤ ማድረግ፣
- በፀረ-ኤድስ እንቅስቃሴ ዙሪያ ኘሮጀክቶችን መቅረፅና ድጋፍ በማፈላለግ ተግባራዊ ማድረግ፣

- የመረጃ፣ ትምህርትና ስርፀት / የባህሪ ለውጥ ሥርፀት ( IEC/BCC ) ማቴሪያሎችን ማዘጋጀት ወይም ማሰባሰብና ማሰራጨት፣

- ኤች.አይ.ቪ/ኤድስን በሚመለከት የሚወጡ ፖሊሲዎችና መርህ ግብሮች፣ መመሪያዎች፣ አዋጆችና ደንቦችን ለህብረተሰቡ ማስተዋወቅ፣
- የተሻለ የፀረ ኤድስ እንቅስቃሴ ካላቸው ክፍሎች ጋር የልምድ ልውውጥ ማድረግ፣
- በፀረ ኤድስ እንቅስቃሴ ዙሪያ ከተሰማሩ አካላት ጋር በቅንጅት መስራት፣
- የኤች.አይ.ቪ/ኤድስን ስርጭት፣ ገፅታ፣ ማኅበረ ኢኮኖሚያዊ ተፅእኖና የህብረተሰቡን የባህሪይ ለውጥ በሚመለከት ጥናታዊ ሥራ መስራት፣ግኝቱንም ማስተዋወቅ፣
- በዘርፉ በሚደረገው የፀረ ኤድስ እንቅስቃሴ የሚገኘውን ለውጥ በየጊዜው መገምገም፣
- የተከናወኑ የፀረ ኤድስ ተግባራትን በወቅቱ ለሚመለከተው አካል ሪፖርት ማድረግ፣

የአብክመ የኤች.አይ.ቪ/ኤድስ መከ/መቆ/ ሴክሬታሪያት

***የወደፊት ተስፋችን ከኤድስ ነፃ የሆነ ህብረተሰብ መገንባት ነው!***

## 6. ማስታወቂያና ህዝብ ግንኙነት

ኅብረተሰባችን ስለ ኤች.አይ.ቪ/ኤድስ አደገኛነትና ስለሚያስከትለው ዙሪያ መለስ ተፅእኖ ያለው ግንዛቤና የባህሪይ ለውጥ ዝቅተኛ መሆኑ አጠያያቂ አይደለም፡፡ ለዚህም በምክንያት ከሚጠቀሱት ውስጥ ስለበሽታው በቂ መረጃ ያለማግኘትና የተለያዩ ስልቶችን በመጠቀም ተከታታይነት ያለው የፀረ ኤድስ እንቅስቃሴ አለመደረጉ ነው፡፡ በመሆኑም ይህ ዘርፍ ኤች.አይ.ቪ/ኤድስን በሚመለከት ትክክለኛና ወቅታዊ መረጃዎችን በማቅረብ የኅብረተሰባችንን ግንዛቤ በማሳደግ በኩል አመርቂ እንቅስቃሴ ማድረግ የሚጠበቅበት ሲሆን እንዲሁም የፀረ-ኤድስ እንቅስቃሴዎችን

ለህብረተሰቡ በማሳወቅ የበኩሉን ሚና ሊጫወት እንደሚችል ይታመናል፡፡ በመሆኑም ዘርፉ የሚከተሉትን ተግባራት ሊያከናውን እንደሚችል ይጠበቃል፡፡

## ተግባራት

- በዘርፉ ፀረ-ኤድስ እንቅስቃሴዎችን ማቀድና ከመደበኛ ሥራው ጋር በማጣመር ተግባራዊ የሚሆንበትን መንገድ ማመቻቸት፣
- በስሩ በየደረጃው በሚገኙ ጽ/ቤቶች የፀረ ኤድስ እንቅስቃሴን የሚከታተል ባለሙያ /Focal person/ መሰየም፣
- የተለያዩ ሚዲያዎችን በመጠቀም ህብረተሰቡ ስለኤች አይ ቪ/ኤድስ በቂ ግንዛቤ እንዲኖረው ማድረግ እንዲሁም ሠራተኛው ራሱንና ቤተሰቡን ከበሽታው እንዲጠብቅ የተጠናከረና ተከታታይነት ያለው ትምህርት መስጠት፣
- የተለያዩ የተቀረፁ የምስልና የድምፅ የፀረ ኤድስ ካሴቶችን በማፈላለግና በማዘጋጀት ስራ ላይ ማዋል፣
- በፀረ-ኤድስ እንቅስቃሴ ዙሪያ የሚከናወኑ ተግባራትን በቂ የሆነ የሚዲያ ሽፋን መስጠትና ለመረጃና ማገናዘቢያነት ዝግጁ ማድረግ፣
- ለኤች.አይ.ቪ/ኤድስ መስፋፋት ምክንያት የሆኑትን ጎጂ ባህላዊና ልማዳዊ ድርጊቶች እንዲወገዱ ጥረት ማድረግ፣
- ህብረተሰቡ በፈቃደኝነት ላይ የተመሰረተ የኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ደም ምርመራ እንዲያደርግ ማበረታታትና ማስተማር፣
- በየደረጃው ለሚገኙ የዘርፉ ሠራተኞች ኤች.አይ.ቪ/ኤድስን በሚመለከት የተለያዩ ስልጠናዎችን መስጠትና ተግባራዊነቱን መከታተል፣



- ከቫይረሱ ጋር ለሚኖሩ፣ ለኤድስ በሽተኞችና በኤድስ ምክንያት ወላጆቻቸውን ላጡ ልጆች የተለያዩ የገቢ ማሰባሰቢያ ኘሮግራሞችን በማዘጋጀት ድጋፍና እንክብካቤ ማድረግ፣
- በፀረ ኤድስ እንቅስቃሴ ዙሪያ ኘሮጀክቶችን መቅረፅና ድጋፍ በማፈላለግ ተግባራዊ ማድረግ፣
- የመረጃ፣ ትምህርትና ስርፀት / የባህሪ ለውጥ ሥርፀት ( IEC/BCC ) ማቴሪያሎችን ማዘጋጀትና ወይም ማሰባሰብና ማሰራጨት፣
- ኤች.አይ.ቪ/ኤድስን በሚመለከት የሚወጡ ፖሊሲዎች፣ መርህ ግብሮች፣ መመሪያዎች፣ አዋጆችና ደንቦችን ለህብረተሰቡ ማስተዋወቅ፣ የማሻሻያ ሀሳቦችን ማፍለቅ፣
- የተሻለ የፀረ-ኤድስ እንቅስቃሴ ካላቸው ክፍሎች ጋር የልምድ ልውውጥ ማድረግና የተሻለ የስራ አፈፃፀም ያላቸውን በመለየት በአስተማሪነታቸው ለሌሎች ማስተዋወቅ፣
- በፀረ ኤድስ እንቅስቃሴ ዙሪያ ለተሰማሩ አካላት ሙያዊ ድጋፍ መስጠትና ተቀናጅቶ መስራት፣
- የኤች.አይ.ቪ/ኤድስን ስርጭት፣ የተፅእኖ ገፅታና የህብረተሰቡን የባህሪይ ለውጥ በሚመለከት ጥናታዊ ስራ መስራት፣ ግኝቱንም ማስተዋወቅ፣
- በዘርፉ በሚደረገው የፀረ-ኤድስ እንቅስቃሴ የሚገኘውን ለውጥ መገምገም፣
- የተከናወኑ የፀረ-ኤድስ ተግባራትን በወቅቱ ለሚመለከተው አካል ሪፖርት ማድረግ፡፡

# የኤች.አይ.ቪ ቫይረስ በደማቸው ውስጥ ላለባቸው ሰዎች ፍቅርና እንክብካቤ እንስጣቸው!

## 7. ሠራተኛና ማኅበራዊ ጉዳይ

በአገራችን አብዛኛው ህዝብ የሚተዳደረው በግብርና ሲሆን በቁጥር አነስተኛ የሆኑ ሠራተኞች በማምረቻና ሌሎች ተቋማት ተሠማርተው የሚገኙ ናቸው:: በዚህ ላይ በከተሞች አካባቢ ከ15-49 ባሉ ዕድሜ ለሚሞቱ ሠዎች ተጠቃሹ ምክንያት ኤድስ ሲሆን ይህ የሚያመላክተው የችግሩ ገፈት ቀማሾች በየፋብሪካውና በየመስሪያ ቤቱ ተሠማርተው ከፍተኛ የሥራ ድርሻ በማበርከት ላይ ያሉ ሠራተኞች መሆናቸውን ነው:: ይህ የአምራች ኃይል ዕጦት በአገሪቱ ላይ የሚያስከትለው የማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ቀውስ ከፍተኛ ነው::

የአብክመ የኤች.አይ.ቪ/ኤድስ መከ/መቆ/ ሴክሬታሪያት

ስለዚህ የሠራተኛና ማኅበራዊ ጉዳይ ዘርፍ ካለው የሥራ ድርሻ አንፃር ኤች.አይ.ቪ/ኤድስን ለመከላከል የሚከተሉትን ተግባራት መፈፀም ይጠበቅበታል::

### ተግባራት

- በዘርፉ ፀረ-ኤድስ እንቅስቃሴዎችን በማቀድና ከመደበኛ ሥራው ጋር በማጣመር ተግባራዊ የሚሆንበትን መንገድ ማመቻቸት፣
- በዘርፉ በየደረጃው በሚገኙ ጽ/ቤቶች የፀረ ኤድስ እንቅስቃሴን የሚያስተባብር ባለሙያ /Focal Person/ መሰየም፣
- በዘርፉ የሚገኙ ሠራተኞችና ከሥራው ጋር ግንኙነት ያላቸው የኅብረተሰብ ክፍሎች ራሳቸውንና ቤተሰቦቻቸውን ከበሽታው እንዲጠበቁ የተጠናከረ የፀረ ኤድስ ሥራ መሥራት፣
- ለኤች.አይ.ቪ/ኤድስ መስፋፋት ምክንያት የሆኑ ጎጂ ባህላዊና ልማዳዊ ድርጊቶችን መለየትና እንዲወገዱ ጥረት ማድረግ፣
- በዘርፉ የሚገኙ ሠራተኞችና ከሥራው ጋር ግንኙነት ያላቸው የህብረተሰብ ክፍሎች በፈቃደኝነት ላይ የተመሠረተ የኤች.አይ.ቪ ደም ምርመራ እንዲያደርጉ ማበረታታትና ሁኔታዎችን ማመቻቸት፣
- ከኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ጋር የሚኖሩ ሠራተኞች በሥራ አካባቢ የሚደርስባቸውን ችግር ለማወቅ የሚያስችል አሠራር መዘርጋት፣
- የሠራተኛ ማኅበራት መሪዎችን፣ ሠራተኛውንና ቤተሰብን ያካተተ ሠፊ የግንዛቤና የባህሪ ለውጥ የሚያመጣ የትምህርትና ቅስቀሳ ሥራዎችን ማከናወን፣

- የሙያ ደህንነትና ጥበቃ በሥራ ቦታና አካባቢ በተገቢው ሁኔታ ተግባራዊ እንዲሆን በማስተማር በሥራ አጋጣሚዎች ለቫይረሱ የመጋለጥ አደጋን መቀነስ፣
- አረጋውያንና አካል ጉዳተኞች ኤች.አይ.ቪ/ኤድስን በመከላከሉ ሥራ ተሳታፊ እንዲሆኑ ማበረታታትና ራሳቸውን እንዲጠብቁ ማድረግ፣
- ለኤች.አይ.ቪ/ኤድስ መስፋፋት ምክንያት የሆኑ ማኅበራዊ ጠንቆችን በመለየት ትኩረት ሰጥቶ መንቀሳቀስ፣
- አሠሪዎች ለሠራተኞቻቸው የሕክምና አገልግሎት ድጋፍ ስምምነት እንዲያደርጉላቸው ሁኔታዎችን ማመቻቸት፣
- በማኅበራዊ ችግር ምክንያት የበለጠ ለኤድስ የሚጋለጡ የህብረተሰብ ክፍሎች /ሴተኛ አዳሪዎች ፣ የጎዳና ተዳዳሪዎች/ ራሳቸውን ከበሽታው እንዲጠብቁ አስፈላጊውን ድጋፍ ማድረግ፣
- የፀረ ኤድስ ኘሮጀክቶች በመቅረጽ ድጋፍ ማፈላለግና ተግባራዊ ማድረግ
- ከቫይረሱ ጋር ለሚኖሩ፣ ለኤድስ ህሙማን እና በኤድስ ምክንያት ወላጆቻቸውን ላጡ ልጆች የተለያዩ የገቢ ማስባሰቢያ ኘሮግራሞችን በማዘጋጀት ድጋፍና እንክብካቤ ማድረግ፣
- በዘርፉ የሚገኙ ባለሙያዎች የኘሮጀክት ሀሳቦችን በማመንጨት በየደረጃው ለሚገኙ የፀረ ኤድስ ኮሚቴዎች ሙያዊ ድጋፍ ማድረግ፣
- የመረጃ፣ ትምህርትና ሥርፀት/ የባህሪ ለውጥ ሥርፀት ( IEC/BCC ) ማቴሪያሎችን በማዘጋጀት ወይም በማሰባሰብ ማሠራጨት፣
- ኤች.አይ.ቪ/ኤድስን በሚመለከት የሚወጡ ፖሊሲዎች ፣ መርሃ ግብሮች ፣ መመሪያዎች ፣ አዋጆችና ደንቦችን ለህብረተሰቡ ማስተዋወቅ፣



- ኤች.አይ.ቪ/ኤድስን በሚመለከት የተለያዩ ሥልጠናዎች መስጠትና ተግባራዊነቱን መከታተል፣
- የተሻለ የፀረ-ኤድስ እንቅስቃሴ ካላቸው ክፍሎች ጋር የልምድ ልውውጥ ማድረግ፣
- በፀረ ኤድስ እንቅስቃሴ ዙሪያ ከተሠማሩ አካላት ጋር በቅንጅት መስራት፣
- የኤች.አይ.ቪ/ኤድስን ስርጭት፣ ገጽታ፣ ማኅበራዊ ተፅእኖና የህብረተሰቡን የባህሪ ለውጥ በሚመለከት ከሚመለከታቸው ጋር በመተባበር ጥናታዊ ስራ መሥራት፣ግኝቱንም ማሰራጨት፣
- በዘርፉ በተደረገው የፀረ ኤድስ እንቅስቃሴ የተገኘውን ለውጥ መገምገም፣
- የተከናወኑ የፀረ-ኤድስ ተግባራትን በወቅቱ ለሚመለከተው አካል ሪፖርት ማድረግ::

**ኤድስን መከላከል ይቻላል !**

## 8. ንግድ፣ ኢንዱስትሪና ከተማ ልማት

የኤች.አይ.ቪ/ኤድስ መስፋፋት አስጊነቱ ደረስ የአገራችን የንግድ እንቅስቃሴና የኢንዱስትሪ መስፋፋት አደጋ ላይ ስለሚወድቅ ዕድገታችን የታሠበውን ያህል ለውጥ ሊያመጣ አይችልም::

በመሆኑም ከዘርፉ ጋር በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ግንኙነት ያላቸው ነጋዴዎች፣ ባለሀብቶች፣ አሽከርካሪዎችና ሌሎች በዘርፉ ተሳታፊ የህብረተሰብ ክፍሎችን ከበሽታው ለመከላከል የሚከተሉትን ተግባራት በዚህ ዘርፍ መፈፀም ይጠበቃል::

## ተግባራት

- በዞርፉ ፀረ-ኤድስ እንቅሰቃሴዎችን ማቀድና ከመደበኛ ሥራው ጋር በማጣመር ተግባራዊ የሚሆንበትን መንገድ ማመቻቸት፣
- በዞርፉ በየደረጃው በሚገኙ ጽ/ቤቶችና ማህበራት የፀረ ኤድስ እንቅስቃሴን የሚያስተባብር ባለሙያ /Focal Person/ መሰየም፣
- በዞርፉ የሚገኙ ሠራተኞች ከሥራው ጋር ግንኙነት ያላቸው የህብረተሰብ ክፍሎች ራሳቸውንና ቤተሰቦቻቸውን ከበሽታው እንዲጠ ብቁ የተጠናከረ የፀረ ኤድስ ሥራ መስራት፣
- በዞርፉ የሚገኙ ሠራተኞችና ከሥራው ጋር ግንኙነት ያላቸው የህብረተሰብ ክፍሎች በፈቃደኝነት ላይ የተመሠረተ የኤች.አይ.ቪ ደም ምርመራ እንዲያደርጉ ማበረታታትና ሁኔታዎችን ማመቻቸት፣
- ከሚመለከታቸው ጋር በመቀናጀት ለመጠጥ ቤቶች እና ለሆቴሎች በቂ የሆነ የኮንዶም አቅርቦት የሚቀርብበትን ሁኔታ ማመቻቸት፣

- በአውቶቡስ መናኸሪያዎች፣ በማኅበር በተደራጁ የትራንስፖርት ድርጅቶችና በኢንዱስትሪ ተቋማት ላይ ትኩረት በማድረግ የተጠናከረ የፀረ ኤድስ እንቅስቃሴ ማድረግ፣
- በንግድ ፈቃድ ሽፋን ኤች.አይ.ቪ/ኤድስን ሊያስፋፉ የሚችሉ እንቅስቃሴዎች መከታተልና ሕጋዊ ዕርምጃ እንዲወሰድባቸው ማድረግ፣
- ኤች.አይ.ቪ/ኤድስን በሚመለከት የተለያዩ ሥልጠናዎች መስጠትና ተግባራዊነቱን መከታተል፣

የአብክመ የኤች.አይ.ቪ/ኤድስ መከ/መቆ/ ሴክሬታሪያት

- ከቫይረሱ ጋር ለሚኖሩ ፣ ለኤድስ ህሙማንና በኤድስ ምክንያት ወላጆቻቸውን ላጡ ልጆች የተለያዩ የገቢ ማሰባሰቢያ ኘሮግራሞችን በማዘጋጀት ድጋፍና እንክብካቤ ማድረግ፣
- በፀረ-ኤድስ እንቅሰቃሴ ዙሪያ ኘሮጀክቶችን መቅረጽና ድጋፍ በማፈላለግ ተግባራዊ ማድረግ ፣
- በዞርፉ የሚገኙ ባለሙያዎች የኘሮጀክት ኃሳቦችን በማመንጨት በየደረጃው ለሚገኙ የፀረ ኤድስ ኮሚቴዎችና ማህበራት ሙያዊ ድጋፍ ማድረግ፣
- የመረጃ፣ ትምህርትና ስርፀት /የባህሪ ለውጥ ሥርፀት ( IEC/BCC ) ማቴሪያሎችን በማዘጋጀት ወይም በማሰባሰብ ማሠራጨት፣
- ኤች.አይ.ቪ/ኤድስን በሚመለከት የሚወጡ ፖሊሲዎች፣ መርሃ ግብሮች፣ መመሪያዎች አዋጆችና ደንቦችን ለህብረተሰቡ ማስተዋወቅ፣
- የንግድ ም/ቤቶች በኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ዙሪያ የተጠናከረ ሥራ እንዲሠሩ ማበረታታትና አስፈላጊውን ዕገዛ ማድረግ፣
- የተሻለ የፀረ-ኤድስ እንቅስቃሴ ካላቸው ክፍሎች ጋር የልምድ ልውውጥ ማድረግ፣
- በፀረ-ኤድስ እንቅሰቃሴ ዙሪያ ከተሠማሩ አካላት ጋር በቅንጅት መስራት ፣
- የኤች.አይ.ቪ/ኤድስን ሥርጭት፣ ገጽታ፣ አሉታዊ ተፅእኖና የህብረተሰቡን የባህርይ ለውጥ በሚመለከት ከሚመለከታቸው ጋር በመሆን ጥናታዊ ሥራ መስራት፣ ውጤቱንም ማሠራጨት፣
- በዞርፉ በተደረገው የፀረ ኤድስ እንቅስቃሴ የተገኘውን ለውጥ መገምገም፣

- የተከናወኑ የፀረ-ኤድስ ተግባራትን በወቅቱ ለሚመለከተው አካል ሪፖርት ማድረግ፡፡

# ስለ ኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ከቤተሰባችን ጋር በግልፅ እንወያይ !

## 9. ፍትህ ፀጥታና አስተዳደር

የኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ሥርጭት መከላከልና መቆጣጠርን የተሟላ ለማድረግ የፍትህ አካላት የሚጫወቱት ሚና ቀላል አይደለም፡፡ በተለይም ከቫይረሱ ጋር የሚኖሩና የኤድስ ህሙማን የሚደርስባቸውን የመብት መጓደልና የመገለል ችግር ማቃለል የሚቻለው ሰብዓዊ መብቶቻቸውን ማስከበር ሊቻል ብቻ መሆኑ ግልጽ ነው፡፡ ይህም የቫይረሱ ተጠቂዎችን በምናካሂደው የመከላከልና የቁጥጥር ሥራ ተሳታፊ ለማድረግ ከማስቻሉም በላይ ለሥራችን ውጤታማነት አጋዥነት አለው፡፡ በመሆኑም



በዘርፉ ኤች.አይ.ቪ/ኤድስን በመከላከሉ ጥረት የሚከተሉትን ተግባራት ማከናወን ተገቢ ይሆናል፡፡

### ተግባራት

- በዘርፉ ፀረ-ኤድስ እንቅስቃሴዎችን ማቀድና ከመደበኛ ሥራው ጋር በማጣመር ተግባራዊ የሚሆንበትን መንገድ ማመቻቸት፣
- በዘርፉ በየደረጃው በሚገኙ ጽ/ቤቶች የፀረ-ኤድስ እንቅስቃሴን የሚከታተል ባለሙያ /Focal Person/ መሰየም፣
- በዘርፉ የሚገኙ ሠራተኞችና ከሥራው ጋር ግንኙነት ያላቸው የህብረተሰብ ክፍሎች ራሳቸውንና ቤተሰቦቻቸውን ከበሽታው እንዲጠበቁ የተጠናከረ የፀረ-ኤድስ ሥራ መስራት፣
- በዘርፉ የሚገኙ ሠራተኞችና ከሥራው ጋር ተያያዥነት ያላቸው የህብረተሰብ ክፍሎች በፈቃደኝነት ላይ የተመሠረተ የኤች.አይ.ቪ. ደም ምርመራ እንደያደርጉ ማበረታታና ሁኔታዎችን ማመቻቸት፣
- በየደረጃው ያሉ የሕግ አካላት ከቫይረሱ ጋር ለሚኖሩና ለኤድስ በሽተኞች የሰብዓዊ መብት መከበር የበኩላቸውን ጥረት ማድረግ፣
- በደማቸው ውስጥ ኤች.አይ.ቪ. ያለባቸው ግለሰቦች በሽታውን ሆን ብለው ወደ ጤነኛ ሠዎች የሚያስተላልፉትን በመከታተል ሕጋዊ ዕርምጃ እንዲወሰድባቸው ማድረግና ህብረተሰቡ እንዲያውቀው ማድረግ፣
- ኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ሥርጭትን የሚያባብሱ ምክንያቶች፣ ለምሳሌ አስገድዶ መድፈር፣ ጠለፋና የመሳሰሉትን በቅድመ ወንጀል መከላከል ሥራዎች ላይ ያተኮረ የተጠናከረ እንቅስቃሴዎችን ማከናወን፣
- የአደንዛዥ ዕፅ ዝውውሮችንና ሕገ ወጥ ቪዲዮ ቤቶችን መቆጣጠርና በህገ ወጦች ላይ ሕጋዊ ዕርምጃ መውሰድ፣

- ልዩ ሁኔታዎች እስከሌሉ ድረስ የኤች.አይ.ቪ ደም ምርመራ የሚደረገው በተመርማሪው ሙሉ ፈቃደኝነት መሆኑን ማረጋገጥ፣
- አሁን በሥራ ላይ ያሉ ህጎች ደንቦችና መመሪያዎችን ከኤች.አይ.ቪ/ኤድስና ከአባላዘር በሽታዎች ጋር በማገናዘብ እንዲሻሻሉና እንዲጠናከሩ ማድረግ፣
- ከሴቶች መብት ጥበቃ ጋር የተገናኙ ህጎችና ደንቦች በየደረጃው እንዲሻሻሉና ተግባራዊ እንዲሆኑ የሚመለከታቸውን አካላት ማሳተፍ፣
- ማንኛውም ኤች.አይ.ቪ/ኤድስን አስመልክቶ የሚደረግ የምርምርና ሥርፀት ሥራ የአገሪቱን ህጎች ፣ ደንቦችና የሥነ ምግባር ደረጃዎች መጠበቁን ማረጋገጥ፣
- ኤች.አይ.ቪ/ኤድስን በተመለከተ የወጡትን ህጎች፣ደንቦችና መመሪያዎች በፍትህ አካላት በየደረጃው መተግበራቸውን መከታተል፣
- ከቫይረሱ ጋር ለሚኖሩ ለኤድስ ህሙማንና በኤድስ ምክንያት ወላጆቻቸውን ላጡ ልጆች የተለያዩ የገቢ ማሰባሰቢያ ኘሮግራሞች በማዘጋጀት ድጋፍና እንክብካቤ ማድረግ፣
- ኤች.አይ.ቪ/ኤድስን በሚመለከት የተለያዩ ሥልጠናዎችን በመስጠት ተግባራዊነቱን መከታተል፣
- በፀረ-ኤድስ እንቅስቃሴ ዙሪያ ኘሮጀክቶችን መቅረጽና ድጋፍ በማፈላለግ ተግባራዊ ማድረግ፣
- በዘርፉ የሚገኙ የህግ ባሙያዎች የኘሮጀክት ኃሳቦችን በማመንጨት በየደረጃው ለሚገኙ የፀረ ኤድስ ኮሚቴዎች ሙያዊ ድጋፍ ማድረግ፣
- የመረጃ፣ ትምህርትና ሥርፀት /የባህሪ ለውጥ ሥርፀት ( IEC/BCC ) ማቴሪያሎችን በማዘጋጀት ወይም በማሰባሰብ ማሠራጨት፣



- ኤች.አይ.ቪ/ኤድስን በሚመለከት የሚወጡ ፖሊሲዎች፣ መርህ ግብሮች ፣ መመሪያዎች፣ አዋጆችና ደንቦችን ለህብረተሰቡ ማስተዋወቅ፣
- የተሻለ የፀረ-ኤድስ እንቅስቃሴ ካላቸው ክፍሎች ጋር የልምድ ልውውጥ ማድረግ፣
- በፀረ-ኤድስ እንቅስቃሴ ዙሪያ ከተሠማሩ አካላት ጋር በቅንጅት መስራት፣
- የኤች.አይ.ቪ/ኤድስን ሥርጭት ገጽታና ተፅእኖውን እንዲሁም የህብረተሰቡን የባህሪይ ለውጥ በሚመለከት ከሚመለከታቸው ጋር በመሆን ጥናታዊ ሥራ መስራት፣ግኝቱንም ማሠራጨት፣
- በዘርፉ በሚደረገው የፀረ-ኤድስ እንቅስቃሴ የሚገኘውን ለውጥ መገምገም፣ ድክመቶችን ማረም፣
- የተከናወኑ የፀረ-ኤድስ ተግባራትን በወቅቱ ለሚመለከተው አካል ሪፖርት ማድረግ::

## 10. የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት

እንደሚታወቀው ኤች.አይ.ቪ/ኤድስን ለመከላከልና ለመቆጣጠር የመንግሥት፣ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችና የህብረተሰቡ ከፍተኛ ተሳትፎ ያስፈልጋል:: ይህንንም ዘርፈ ብዙ ተሳትፎ ሥርዓት ባለው መንገድ አቀናጅቶ ለመምራት በዕቅድና በበጀት የተደገፈ የፀረ ኤድስ እንቅስቃሴ ሊኖር ይገባል:: በመሆኑም ይህ ዘርፈ ብዙ እንቅስቃሴ የሁሉንም ዘርፎች ትኩረት እንደያገኝ የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ከፍተኛ የማስተባበር

ሚና የሚኖረው ከመሆኑም በላይ ዘርፉ በዚህ ረገድ የበኩሉን አስተዋጽኦ ለማድረግ የሚከተሉትን ተግባራት ሊያከናውን እንደሚገባ ይታመናል፡፡

**ተግባራት**

- በዘርፉ ፀረ ኤድስ እንቅስቃሴዎችን ማቀድና ከመደበኛ ሥራው ጋር በማጣመር ተግባራዊ የሚሆንበትን መንገድ ማመቻቸት፣
- በዘርፉ በየደረጃው በሚገኙ ጽ/ቤቶች ከመደበኛ ሥራው በተጨማሪ የፀረ-ኤድስ እንቅስቃሴን የሚከታተል ባለሙያ /Focal Person/ መመደብ፣
- በዘርፉ የሚገኙ ሠራተኞችና ከሥራው ጋር ግንኙነት ያላቸው የህብረተሰብ ክፍሎች ራሳቸውንና ቤተሰቦቻቸውን ከበሽታው እንዲጠበቁ የተጠናከረ የፀረ ኤድስ ሥራ መስራት፣
- በዘርፉ የሚገኙ ሠራተኞችና ከሥራው ጋር ግንኙነት ያላቸው የህብረተሰብ ክፍሎች በፈቃደኝነት ላይ የተመሠረተ የኤች.አይ.ቪ ደም ምርመራ እንዲያደርጉ ማበረታታትና ሁኔታዎችን ማመቻቸት፣
- የኤች.አይ.ቪ/ኤድስን መከላከልና መቆጣጠር ተግባራት በእያንዳንዱ ሴክተር መ/ቤቶች ዓመታዊ የሥራ ዕቅድ ውስጥ መካተታቸውን ማረጋገጥና በበጀት በመደገፍ ረገድም ዕገዛ ማድረግ፣
- በፀረ-ኤድስ እንቅስቃሴ ዙሪያ ተሠማርተው የአቅም ማነስ ላለባቸው ክፍሎች የሂሳብ አያያዝና የኘሮጀክት አዘገጃጀት ሥልጠናዎችን መስጠት፣
- የተለያዩ ለጋሽ ድርጅቶች በሽታውን በመከላከል ዙሪያ አስፈላጊውን ዕገዛ እንዲያደርጉ ጥረት ማድረግ፣

የአብክመ የኤች.አይ.ቪ/ኤድስ መከ/መቆ/ ሴክሬታሪያት

- ከቫይረሱ ጋር ለሚኖሩ ለኤድስ ህሙማን እና በኤድስ ምክንያት ወላጆቻቸውን ላጡ ልጆች የተለያዩ የገቢ ማስባሰቢያ ኘሮግራሞችን በማዘጋጀት ድጋፍና እንክብካቤ ማድረግ፣
- በፀረ-ኤድስ እንቅስቃሴ ዙሪያ ኘሮጀክቶችን መቅረጽና ድጋፍ በማፈላለግ ተግባራዊ ማድረግ፣
- የመረጃ ፣ ትምህርትና ሥርፀት /የባህሪ ለውጥ ሥርፀት ( IEC/BCC ) ማቴሪያሎችን በማዘጋጀት ወይም በማሰባሰብ ማሠራጨት፣
- ኤች.አይ.ቪ/ኤድስን በሚመለከት የሚወጡ ፖሊሲዎች፣ መርሀ ግብሮች፣ መመሪያዎች፣ አዋጆችና ደንቦችን ለህብረተሰቡ ማስተዋወቅና የፖሊሲ ኃሳቦችን ማመንጨት፣
- በፀረ-ኤድስ እንቅስቃሴ ዙሪያ ከተሰማሩ አካላት ጋር በቅንጅት መሥራት፣
- የኤች.አይ.ቪ/ኤድስን ሥርጭት ገጽታና ዘርፈ ብዙ ተፅእኖውን እንዲሁም የህብረተሰቡን የባህርይ ለውጥ በሚመለከት የቅኝትና ጥናታዊ ሥራ መስራት፣ውጤቱንም ማሠራጨት፣
- በዘርፉ በሚደረገው የፀረ ኤድስ እንቅስቃሴ የሚገኘውን ለውጥ በመገምገም፣ድክመቶችን ማረም፣
- የተከናወኑ የፀረ-ኤድስ ተግባራትን በወቅቱ ለሚመለከተው አካል ሪፖርት በማድረግ እንቅስቃሴው ተገቢውን ትኩረት እንዲያገኝ ማድረግ፣

## ኤች.አይ.ቪ/ኤድስ

## *የጤና ችግር ብቻ ሳይሆን የልማትና የዕድገትም እንቅፋት ነው !*

## 11. ህዝብ ተሳትፎና አደረጃጀት

ምንም እንኳ ከአሁን ቀደም በሽታውን ለመከላከልና ለመቆጣጠር የተደረጉ ጅምር ጥረቶች ቢኖሩም ቅንጅታዊ አሠራር የጎደላቸው በመሆናቸው ውጤታቸው ሊለካ የሚችልበትና መላውን ህብረተሰብ ባሳተፈ መንገድ ተካሂደዋል ሊባሉ የሚችሉ አልነበሩም፡፡ ይህም በብዙ መልኩ ሊገለጽ ይችላል፡፡ በአንድ በኩል በአገራችን የተጀመረው ዲሞክራሲያዊ ባህል ገና ያልዳበረ መሆኑ ነው፡፡



በሌላ በኩል ዝቅተኛ የፖለቲካና የኢኮኖሚ ዕድገት ጋር በተያያዘ መልኩ በዝቅተኛ የኑሮና የትምህርት ደረጃ ላይ የምንገኝ በመሆኑ ህዝቡ ተደራጅቶ ሰብዓዊና ዲሞክራሲያዊ መብቶቹን ማስከበር አለመቻሉ የሚጠቀስ ነው፡፡ ያሉንን ተቋማዊ አደረጃጀቶች ከላይ እስከ ታች አንቀሳቅሶ የምንፈልገውን ልማት ለማምጣት በሚያግዝ አኳኋን መጠቀም አለመቻላችን ተያይዞ የሚነሳ ሌላው ድክመታችን ነው፡፡

ስለዚህ ወረርሽኙን በመከላከልና በመቆጣጠር የህዝባችን መተሳሰብና በጋራ የመኖር ጥቅምና ልምድ ተጠቅመን በተናጠልና በግል ከምናደርገው እንቅስቃሴ ይልቅ እንደ ህዝብና ቤተሰብ ተደራጅተን በጋራ መንቀሳቀስ መጀመር ይኖርብናል፡፡ ይህም ለውጤማነታችን አጋዥ ኃይል እንደሚሆን እሙን ነው፡፡ ከዚህ አኳያ የህዝብ ተሳትፎና አደረጃጀት ዘርፍ ግለሠብ ፣ ቤተሰብንና ኅብረተሰቡን በማንቀሳቀስ የሚከተሉትን ተግባራት ማከናወን ይጠበቅበታል፡፡

### ተግባራት

- በዘርፉ ፀረ ኤድስ እንቅስቃሴዎችን ማቀድና ከመደበኛ ሥራው ጋር በማጣመር ተግባራዊ የሚሆንበትን መንገድ ማመቻቸት፣
- በዘርፉ በየደረጃው በሚገኙ ጽ/ቤቶችና ማህበራት ከመደበኛ ሥራው በተጨማሪ የፀረ ኤድስ እንቅስቃሴን የሚከታተል ባለሙያ /Focal Person/ መሰየም፣
- በዘርፉ የሚገኙ ሠራተኞችና ከሥራው ጋር ተያያዥነት ያላቸው የህብረተሰብ ክፍሎች ራሳቸውንና ቤተሰቦቻቸውን ከበሽታው እንዲጠብቁ የተጠናከረ የፀረ ኤድስ ሥራ መስራት፣

- የአርሶ አደር ፣ የወጣቶችና የሴቶች ማኀበራት ኤች.አይ.ቪ/ኤድስ በአባሎቻቸው ላይ እያደረሰ ያለውንና ወደፊት ሊያደርስ የሚችለውን አደጋ በመገንዘብ የተጠናከረ የፀረ ኤድስ እንቅስቃሴ በተከታታይነትና በስፋት እንዲሰሩ ማስቻል፣
- ሴቶች የሥነ ተዋልዶ ጤና ትምህርት አገልግሎት በስፋት እንዲያገኙ ሁኔታዎችን ማመቻቸት፣
- ሴቶች ከኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ጋር ተያያዥነት ያላቸውና ያታ ተኮር ተግባራት ላይ ጠንካራ የአማራር ሚና መጫወት እንዲችሉ ማድረግ ፣ ለምሳሌ በየደረጃው በሚገኙ የፀረ ኤድስ ም/ቤቶችና ኮሚቴዎች ንቁ ተሳትፎ እንዲኖራቸው ማድረግ፣
- በየደረጃው ሴቶችን በገቢ ምንጭ ማስገኛ እንቀሰቃሴዎች እንዲታቀፉ በማድረግ ለሴተኛ አዳሪነት እንዳይዳረጉ ማስቻልና የተዳረጉትንም በሌሎች የሥራ መስኮች እንዲሠማሩ ጥረት ማድረግ፣
- ከቫይረሱ ጋር የሚኖር ሰው ሴቶችን አስገድዶ እንዳይደፍርና በጋብቻ ሰበብም ቫይረሱ ወደ ጤነኛ ሴቶች እንዳያስተላልፍ ልዩ የሕግ ጥበቃና ትኩረት እንዲያገኙ ማድረግ፣
- ከሴቶች መብት ጥበቃ ጋር የተገናኙ ሕጎችና ደንቦች በየደረጃው እንዲሻሻሉና ተግባራዊ እንዲሆኑ የሚመለከታቸውን አካላት ማሳተፍ፣
- በዘርፉ የሚገኙ ሠራተኞችና ከሥራው ጋር ግንኙነት ያላቸው ማኀበራትና የህብረተሰብ ክፍሎች በፈቃደኝነት ላይ የተመሠረተ የኤች.አይ.ቪ ደም ምርመራ እንዲያደርጉ ማበረታታትና ሁኔታዎችን ማመቻቸት፣



- ከቫይረሱ ጋር ለሚኖሩ ወገኖች ለኤድስ ህሙማንና በኤድስ ምክንያት ወላጅ አልባ ለሆኑ ልጆች የተለያዩ የገቢ ማሰባሰቢያ ኘሮግራሞችን በማዘጋጀት ድጋፍና እንክብካቤ ማድረግ፣
- የመረጃ ፣ ትምህርትና ስርፀት / የባህሪ ለውጥ ስርፀት / IEC/BCC/ ማቴሪያሎችን ማሰባሰብና ማሰራጨት፣
- ኤች.አይ.ቪ/ኤድስን በሚመለከት የተለያዩ ሥልጠናዎችን መስጠትና ተግባራዊነቱን መከታተል፣
- በፀረ-ኤድስ እንቅስቃሴ ዙሪያ ኘሮጀክቶችን መቅረጽና ድጋፍ በማፈላለግ ተግባራዊ ማድረግ ፣
- ኤች.አይ.ቪ/ኤድስን በሚመለከት የሚወጡ ፖሊሲዎች፣ መርሃ ግብሮች፣ መመሪያዎች ፣ አዋጆችና ደንቦችን ለህብረተሰቡ ማስተዋወቅ፣
- የተሻለ የፀረ-ኤድስ እንቅሰቃሴ ካላቸው ክፍሎች ጋር የልምድ ልውውጥ ማድረግ፣
- በፀረ-ኤድስ እንቅስቃሴ ዙሪያ ከተሠማሩ አካላት ጋር በቅንጅት መስራት፣
- የኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ሥርጭት ፣ ገጽታና ጉዳቱን እንዲሁም የህብረተሰቡን የባህሪ ለውጥ በሚመለከት ከሚመለከታቸው ጋር በመተባበር የቅኝትና ጥናታዊ ሥራ መስራት፣ ውጤቱንም ማሠራጨት፣
- በዘርፉ በሚደረገው የፀረ-ኤድስ እንቅስቃሴ የሚገኘውን ለውጥ መገምገም፣ድክመቶችን ማረም፣

- የተከናወኑ ፀረ ኤድስ ተግባራትን በወቅቱ ለሚመለከተው አካል ሪፖርት ማድረግ::

# ኤች.አይ.ቪ/ኤድስን መከላከል የሁሉም ዜጋ ኃላፊነት ነው !

## 12. ሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን

በታዳጊ ሀገሮች የልማት እንቅስቃሴ ውስጥ የመንግስት ዘርፍ የሚጫወተው ሚና በምንም የሚተካ አይደለም:: ለዚህም መዋቅራዊ አደረጃጀቱ በቀዳሚነት ተጠቃሽ ሲሆን የመንግሥት ሰራተኞች የሀገርን ልማት ለማፋጠን በሚደረገው ጥረት የበኩላቸውን አስተዋጽኦ እንዲያበረክቱ እራሳቸውን ከኤች አይ ቪ/ኤድስ መጠበቅ እንዳለባቸው



ይታመናል:: ይህ ካልሆነ ግን የሀገራችን የልማት ጥያቄ አጠያያቂ እንደሚሆን የታመነ ነው:: በመሆኑም ይህ ዘርፍ በፀረ ኤድስ እንቅስቃሴ ዙሪያ በየትኛውም ዘርፍ የተሰለፉ የመንግስት ሠራተኞችን በማሳተፍ የሚከተሉትን ተግባራት ሊያከናውን ይጠበቅበታል::

### ተግባራት

- በዘርፉ ፀረ-ኤድስ እንቅስቃሴዎችን ማቀድና ከመደበኛ ሥራው ጋር በማጣመር ተግባራዊ የሚሆንበትን መንገድ ማመቻቸት፣
- በዘርፉ የፀረ-ኤድስ እንቅስቃሴን የሚከታተል ባለሙያ /Focal Person/ መሰየም፣
- በኤድስ ምክንያት የተጎዱ ቤተሰቦች በጉዳይ ማስፈፀም ዙሪያ የሚደርስባቸውን መጉላላትና ችግር ለማስወገድ ከሚመመለከተው ጋር በመሆን መፍትሔ እንዲያገኝ ማድረግ፣
- በሰራተኛው ዘንድ የሚከሰቱ የሞት አደጋዎችን ከአለፉት አመታት ጋር በማነፃፀር ከበሽታው ጋር ያለውን ቁርኝት በመተንተን፣ ሁኔታውን ግልፅ ማድረግና ለፖሊሲ አውጭ አካል በማቅረብ የቅስቀሳ ስራ መስራት ፣ በሽታውን ለመከላከል የሚደረገውን ጥረት ማጠናከር፣
- በተለያዩ የመንግስት መስሪያ ቤቶች በአሁኑ ወቅት እየተሰራባቸው ያሉትን የመንግስት ሰራተኞች መተዳደሪያ ደንቦችና መመሪያዎችን ከኤች.አይ.ቪ/ኤድስ አንፃር በመቃኘትና በመከለስ ወቅታዊ እንዲሆን ጥረት ማድረግ፣

- በዘርፉ የገቢ ማስገኛ ፕሮግራሞችን በማዘጋጀት ከቫይረሱ ጋር ለሚኖሩ ወገኖች፣ ለኤድስ ህሙማንና በኤድስ ምክንያት ወላጆቻቸውን ላጡ ልጆች እክብካቤና ድጋፍ ማድረግ፣
- በዘርፉ የሚገኙ ሠራተኞችና ከስራው ጋር ግንኙነት ያላቸው የህብረተሰብ ክፍሎች በፈቃደኝነት ላይ የተመሠረተ የደም ምርመራ እንዲያደርጉ መቀስቀስና ማበረታታት፣ ሁኔታዎችን ማመቻቸት፣
- ፀረ-ኤድስ ኘሮጀክቶችን በመቅረፅና ለሚመለከታቸው በማቅረብ ድጋፍ ማፈላለግና ተግባራዊ ማድረግ፣
- በኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ዙሪያ የተለያዩ ስልጠናዎችን መስጠትና ውጤታማነቱን መከታተል፣
- የመረጃ፣ ትምህርትና ስርፀት/ የባህሪ ለውጥ ሥርፀት ( IEC/BCC ) ማቴሪያሎችን በማዘጋጀት ወይም በማሰባሰብ ማሰራጨት፣
- ኤች.አይ.ቪ/ኤድስን በሚመለከት የሚወጡ ፖሊሲዎች፣ መርህግብሮች፣ መመሪያዎች፣ አዋጆችና ደንቦችን ለኅብረተሰቡ ማስተዋወቅ፣
- በዘርፉ በተደረገው የፀረ-ኤድስ እንቅስቃሴ የተገኘውን ለውጥ መገምገም፣
- የተሻለ የፀረ-ኤድስ እንቅስቃሴ ካላቸው ክፍሎች ጋር የልምድ ልውውጥ ማድረግ፣
- በዘርፉ የኤች.አይ.ቪ/ኤድስን ስርጭት፣ ገፅታና ጉዳቱን እንዲሁም የህብረተሰቡን የባህሪ ለውጥ በሚመለከት ከሚመለከታቸው ጋር በመተባበር ጥናታዊ ስራ መስራት፣ ውጤቱንም ማሠራጨት፣
- ከሚመለከታቸው አካላት ጋር የቅንጅት ስራ መስራት፣



- የተከናወኑ ፀረ-ኤድስ ተግባራትን በወቅቱ ለሚመለከተው አካል ሪፖርት ማድረግ::

***ከኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ጋር የሚኖሩትን እና በኤድስ ምክንያት ወላጅ አልባ የሆኑ ወገኖቻችንን እንንከባከብ ! እንደግፍ !***

## 13. አደጋ መከላከልና ዝግጁነት

በአገራችን ለኤች.አይ.ቪ/ኤድስ መስፋፋት ዋናው ምክንያት ድህነትና ኋላቀርነት ነው:: እነዚህ ምክንያቶች ህብረተሰቡን ለስራ አጥነት፣ ተስፋ መቁረጥና ወደአልባሌ እንቅስቃሴዎች እንዲያመራ ሊዳርጉት እንደሚችሉ የታወቀ ነው::

በመሆኑም በሠው ሠራሽና በተፈጥሮ አደጋ የሚፈናቀሉ የህብረተሰብ ክፍሎች ቀላል ግምት የሚሰጣቸው ካለመሆናቸውም በላይ በዚሁ ሳቢያ ለኤች አይ ቪ/ኤድስ በቀላሉ ይጋለጣሉ:: ስለዚህ ይህ ዘርፍ የበሽታውን ስርጭት በመከላከልና በመቆጣጠሩ ረገድ የሚከተለትን ተግባራት ሊያከናውን እንደሚገባ ይታመናል::

**ተግባራት**

- በዘርፉ የፀረ ኤድስ እንቅስቃሴዎችን ማቀድና ተግባራዊ ማድረግ፣
- በዘርፉ በየደረጃው በሚገኙ ጽ/ቤቶች ፀረ-ኤድስ እንቅስቃሴን የሚከታተል ባለሙያ /Focal Person/ መሰየም፣
- በተፈጥሮና ሰው ሰራሽ አደጋ ለተፈናቀሉ ወገኖች ከእርዳታው ጎን ለጎን በኤች.አይ.ቪ/ኤድስ መከላከሉ ዙሪያ የተጠናከረ ስራ መስራት፣
- በክልሉ የሚገኙትን መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች በፀረ-ኤድስ እንቅስቃሴ ዙሪያ የተለየ ትኩረት ሰጥተው እንዲንቀሳቀሱ ማበረታታትና አፈፃፀሙን ከሚመለከታቸው ጋር በመሆን መከታተልና መገምገም ፣



- መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ወደ ክልሉ መጥተው በፀረ-ኤድስ እንቅስቃሴ ዙሪያ የበኩላቸውን እገዛ እንዲያደርጉ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር ጥረት ማድረግና ሁኔታዎችን ማመቻቸት፣
- በዘርፉ የገቢ ማሰባሰቢያ ኘሮግራሞችን በማዘጋጀት ከቫይረሱ ጋር ለሚኖሩ ወገኖች ለኤድስ ህሙማንና በኤድስ ምክንያት ወላጆቻቸውን ላጡ ልጆች ድጋፍና እንክብካቤ ማድረግ፣
- በዘርፉ የሚገኙ ሠራተኞችና ከስራው ጋር ግንኙነት ያላቸው የህብረተሰብ ክፍሎች በፈቃደኝነት ላይ የተመሠረተ የደም ምርመራ እንዲያደርጉ መቀስቀስና ማበረታታት ፣
- ፀረ-ኤድስ ኘሮጀክቶችን በመቅረፅና ለሚመለከታቸው በማቅረብ ድጋፍ ማፈላለግና ተግባራዊ ማድረግ፣
- በኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ዙሪያ የተለያዩ ስልጠናዎችን መስጠትና ተግባራዊነቱን መከታተል፣
- የመረጃ፣ ትምህርትና ስርፀት / የባህሪ ለውጥ ሥርፀት ( IEC/BCC ) ማቴሪያሎችን በማዘጋጀት ወይም በማሰባሰብ ማሰራጨት፣
- ኤች.አይ.ቪ/ኤድስን በሚመለከት የሚወጡ ፖሊሲዎችን፣ መርሃግብሮችን፣ መመሪያዎችን፣ አዋጆችና ደንቦችን ለህብረተሰቡ ማስተዋወቅ፣
- በዘርፉ በተደረገው የፀረ-ኤድስ እንቅስቃሴ የተገኘውን ለውጥ መገምገም፣ እርምት ማድረግ፣
- የተሻለ የፀረ-ኤድስ እንቅስቃሴ ካላቸው ክፍሎች ጋር የልምድ ልውውጥ ማድረግ፣

- በዘርፉ የኤች.አይ.ቪ/ኤድስን ስርጭት፣ ገፅታና ተፅእኖውን እንዲሁም የህብረተሰቡን የባህሪ ለውጥ በሚመለከት ጥናታዊ ስራ መስራት፣ ውጤቱንም ማሠራጨት፣
- ከሚመለከታቸው አካላት ጋር የቅንጅት ስራ መስራት፣
- የተከናወኑ ፀረ-ኤድስ ተግባራትን በወቅቱ ለሚመለከተው አካል ሪፖርት ማድረግ፡፡

***ኤች.አይ.ቪ/ኤድስን ለመከላከል ቅንጅታችንን እናጠናክር !***



## 14. የአስተዳደር ጽ/ቤቶች

በክልል ደረጃ የአብክመ የኤች አይ ቪ/ኤድስን መከላከያና መቆጣጠሪያ ም/ቤትን በይፋ በማቋቋም ቁርጠኝነቱን ከማሳየቱም ባሻገር በየደረጃው የኤች አይ ቪ/ኤድስ መከላከልና መቆጣጠሪያ ጽ/ቤቶችን በማቋቋም በክልል የሚደረጉ ፀረ ኤድስ እንቅስቃሴዎች በማስተባበርና አቀናጅቶ በመምራት ጥረት በማድረግ ላይ መሆኑ ይታወቃል፡፡

በዚህ ዘርፍ በየደረጃው የተቋቋሙት የኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ ም/ቤቶች ተግባርና ኃላፊነት እንደተጠበቀ ሆኖ የመስተዳድር ጽ/ቤቶቹ እንደማንኛውም ሴክተር መስሪያ ቤቶች የሚከተሉትን ተግባራት ሊፈፅሙ ይገባል፡፡

### ተግባራት

- በዘርፉ ፀረ-ኤድስ እንቅስቃሴዎችን ማቀድና ተግባራዊ ማድረግ፣
- በዘርፉ በየደረጃው በሚገኙ ፅ/ቤቶች ፀረ-ኤድስ እንቅስቃሴን የሚከታተል ባለሙያ /Focal Person/ መሰየም፣
- በፀረ-ኤድስ እንቅስቃሴ ዙሪያ ለተሰማሩ መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች፣ ህብረተሰብ አቀፍ ማህበራትና የሃይማኖት ተቋማት እንዲሁም ግለሰቦች አስፈላጊውን እገዛ ማድረግ፣
- የገቢ ማሰባሰቢያ ኘሮግራሞችን በማዘጋጀት ከቫይረሱ ጋር ለሚኖሩ ወገኖች፣ ለኤድስ ህሙማንና በኤድስ ምክንያት ወላጆቻቸውን ሳጡ ልጆች እንክብካቤና ድጋፍ ማድረግ፣

- በዘርፉ የሚገኙ ሠራተኞችና ከስራው ጋር ግንኙነት ያላቸው የህብረተሰብ ክፍሎች በፈቃደኝነት ላይ የተመሠረተ የደም ምርመራ እንዲያደርጉ መቀስቀስና ማበረታታት ፣
- ፀረ-ኤድስ ኘሮጀክቶችን በመቅረፅና ለሚመለከታቸው በማቅረብ ድጋፍ ማፈላለግና ተግባራዊ ማድረግ፣
- በኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ዙሪያ የተለያዩ ስልጠናዎችን መስጠትና ተግባራዊነቱን መከታተል፣
- የመረጃ፣ ትምህርትና ስርፀት/ የባህሪ ለውጥ ስርፀት ( IEC/BCC ) ማቴሪያሎችን ማሰባሰብና ማሰራጨት፣
- ኤች.አይ.ቪ/ኤድስን በሚመለከት የሚወጡ ፖሊሲዎችን፣ መርሃግብሮችን፣ መመሪያዎችን፣ አዋጆችና ደንቦች ለህብረተሰቡ ማስተዋወቅ፣
- የተሻለ የፀረ-አድስ እንቅስቃሴ ካላቸው ክፍሎች ጋር የልምድ ልውውጥ ማድረግ፣
- ከሚመለከታቸው አባላት ጋር የቅንጅት ስራ መስራት፣
- በዘርፉ በተደረገው የፀረ ኤድስ እንቅስቃሴ የተገኘውን ለውጥ መገምገም፣ ችግሮችን መፍታት፣
- የተከናወኑ ፀረ-ኤድስ ተግባራትን ለሚመለከተው አካል ሪፖርት ማድረግ::

**ኤች.አይ.ቪ/ኤድስን ለመከላከልና ለመቆጣጠር ጊዜው አሁን ነው !**

የአብክመ የኤች.አይ.ቪ/ኤድስ መከ/መቆ/ ሴክሬታሪያት

## 15. ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት

በክልላችን የሚገኙ ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት የኤች.አይ.ቪ/ኤድስን ስርጭት በመከላከልና በመቆጣጠሩ ረገድ ከፍተኛ ሚና መጫወት እንዳለባቸው ይታመናል:: ተቋሞቹ በርካታ ቁጥር ያላቸው ወጣቶች መናኸሪያ እንደመሆናቸው በወጣቶች ላይ ያተኮሩ የኤች.አይ.ቪ/ኤድስ መከላከያና ቁጥጥር ተግባራት ላይ አተኩረው መስራት ይገባቸዋል:: በመሆኑም ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት በዚህ ረገድ ከዚህ የሚከተሉትን ተግባራት በዋነኛነት ማከናወን ይጠበቅባቸዋል::

### ተግባራት

- የፀረ-ኤድስ እንቅስቃሴዎችን ማቀድና ከመደበኛ ሥራው ጋር በማጣመር ተግባራዊ የሚሆንበትን መንገድ መቀየስ፣
- መምህራን፣ ተማሪዎችንና ሠራተኞችን ያካተተ ፀረ-ኤድስ ግብረ ኃይል ማቋቋምና ማጠናከር፣
- ለኤች.አይ.ቪ/ኤድስ መከላከልና መቆጣጠር ተግባር ሊውሉ የሚችሉ የጥናትና ምርምር ሥራዎች በማከናወን የተገኙ ውጤቶችን ለሚመለከተውና ለተጠቃሚዎች እንዲደርሱ ማድረግ፣
- ተማሪዎች ለእረፍት ወደየአካባቢያቸው በሚመለሱበት ወቅት የአካባቢያቸውን ህብረተሰብ የሚያስተምሩበትን ሁኔታ ማመቻቸት፣

- ከመንግስት አካላት ጋር በመቀናጀት የገቢ ማሰባሰቢያ ኘሮግራሞችን በማዘጋጀት ከቫይረሱ ጋር ለሚኖሩ ወገኖች፣ ለኤድስ ህመማንና በኤድስ ምክንያት ወላጆቻቸውን ላጡ ልጆች እንክብካቤና ድጋፍ ማድረግ፣
- በየተቋማቱ የሚገኙ መምህራን፣ ተማሪዎች፣ ሠራተኞችና ከስራው ጋር ግንኙነት ያላቸው የህብረተሰብ ክፍሎች በፈቃደኝነት ላይ የተመሠረተ የደም ምርመራ እንዲያደርጉ መቀስቀስና ማበረታታት፣
- ተማሪዎች በቡድን ተደራጅተው ስለኤች.አይ.ቪ/ኤድስ በግልጽ የሚወያዩበትን ሁኔታ ማመቻቸት፣
- ፀረ-ኤድሰ ኘሮጀክቶችን በመቅረጽ ለሚመለከታቸው በማቅርብ ድጋፍ ሲገኝ ተግባራዊ ማድረግ፣
- በኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ዙሪያ የተለያዩ ስልጠናዎችን መስጠትና ተግባራዊነቱን መከታተል፣
- የመረጃ፣ ትምህርትና ስርፀት / የባህሪ ለውጥ ሥርፀት ( IEC/BCC ) ማቴሪያሎችን ማዘጋጀት፣ ማሰባሰብና ማሰራጨት፣
- በተቋሙ ውስጥ በተለይም ሴት ተማሪዎች በኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ላይ ያላቸውን ግንዛቤ እንዲያዳብሩ ጥረት ማድረግ፣
- ኤች.አይ.ቪ/ኤድስን በሚመለከት የሚወጡ ፖሊሲዎችን ፣ መርሃ ግብሮችን፣ መመሪያዎችን፣ አዋጆችንና ደንቦችን ለህብረተሰቡ ማስተዋወቅ፣
- በተቋሙ በሚደረገው የፀረ-ኤድስ እንቅስቃሴ የሚገኘውን ለውጥ መገምገም፣

የአብክመ የኤች.አይ.ቪ/ኤድስ መከ/መቆ/ ሴክሬታሪያት

- የተሻለ የፀረ ኤድስ እንቅሰቃሴ ካላቸው ሌሎች ተቋማት ጋር የልምድ ልውውጥ ማድረግ፡፡
- የኤች.አይ.ቪ/ኤድስን ስርጭት፣ ገጽታና ተፅእኖውን እንዲሁም የህብረተሰቡን የባህሪ ለውጥ በሚመለከት የጥናትና ምርምር ሥራ መስራት፣ ውጤቱንም ማስተዋወቅ፣
- ከሚመለከታቸው አካላት ጋር የቅንጅት ሥራ መስራት፡፡

***ጥንቃቄ የተሞላበት የግብረ ሥጋ ግንኙነት በኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ከመያዝ ያድናል !***

# 16. ሌሎች የመንግስት መስሪያ ቤቶች

የኤድስን ስርጭት ለመከላከልና ለመቆጣጠር ሁሉም ድርጅት በየፊናውና መፍትሔ ነው ብሎ ባመነበት መንገድ የራሱን ሥራ እየሰራ ያለ ቢሆንም የተናጠል ጥረት በመሆኑ የተፈለገውን ውጤት ማስገኘት አልተቻለም፡፡ ስለዚህ መንግስት ፣መያድና ህብረተሰቡ በጋራ በመሆን በሽታውን ለመከላከል የተጠናከረ ሥራ መስራት እንዳለባቸው ስለታመነበት ከላይ ከፍ ብሎ ከተዘረዘሩት ተቋማት ውጭ ያልተጠቀሱ የመንግስት መ/ቤቶች እንደየሥራ ባህሪያቸው ከዚህ የሚከተሉትን ተግባራት ሊያከናውኑ ይገባቸዋል፡፡

## ተግባራት

- እንደየመስሪያ ቤቱ የሥራ ባህሪና ተግባር የፀረ-ኤድስ እንቅስቃሴዎችን ማቀድና ተግባራዊ ማድረግ፣
- በየደረጃው በሚገኙ መ/ቤቶች ፀረ-ኤድስ እንቅስቃሴን የሚከታተል ባለሙያ /Focal Person/ መሰየም፣
- ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመቀናጀት የገቢ ማሰባሰቢያ ኘሮግራሞችን በማዘጋጀት ከቫይረሱ ጋር ለሚኖሩ ወገኖች፣ ለኤድስ ህሙማንና በኤድስ ምክንያት ወላጆቻቸውን ላጡ ልጆች እንክብካቤና ድጋፍ ማድረግ፣
- በመስሪያ ቤቱ የሚገኙ ሠራተኞችና ከስራው ጋር ግንኙነት ያላቸው የህብረተሰብ ክፍሎች በፈቃደኝነት ላይ የተመሠረተ የደም ምርመራ እንዲያደርጉ መቀስቀስና ማበረታታት፣



- ፀረ-ኤድስ ኘሮጀክቶችን በመቅረጽና ለሚመለከታቸው በማቅረብ ድጋፍ ማፈላለግ ተግባራዊ ማድረግ፣
- በኤች.አይ.ቪ ኤድስ ዙሪያ የተለያዩ ስልጠናዎች መስጠትና ተግባራዊነቱን መከታተል፣
- የመረጃ፣ ትምህርትና ስርፀት / የባህሪ ለውጥ ሥርፀት ( IEC/BCC ) ማቴሪያሎችን ማዘጋጀት ወይም ማሰባሰብና ማሰራጨት፣
- ኤች.አይ.ቪ/ኤድስን በሚመለከት የሚወጡ ፖሊሲዎችን መርሃ ግብሮችን፣ መመሪያዎችን፣ አዋጆችንና ደንቦችን ለህብረተሰቡ ማስተዋወቅ፣
- የተሻለ የፀረ-ኤድስ እንቅስቃሴ ካላቸው መስሪያ ቤቶች ጋር የልምድ ልውውጥ ማድረግ፣
- የኤች.አይ.ቪ/ኤድስን ስርጭት ገጽታ ተፅእኖ እንዲሁም የህብረተሰቡን የባህሪ ለውጥ በሚመለከት ጥናታዊ ሥራ መስራት፣ ውጤቱንም ማስተዋወቅ፣
- ከሚመለከታቸው አካላት ጋር የቅንጅት ሥራ መስራት፣
- በመስሪያ ቤቱ በተደረገው የፀረ-ኤድስ እንቅስቃሴ የተገኘውን ለውጥ መገምገም፣
- የተከናወኑ የፀረ-ኤድስ ተግባራት ለሚመለከተው አካል ሪፖርት ማድረግ፡፡

**በመተሳሰብ እንፋቀር !**

# 17. መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች
## ( NGOs )

መንግሥት በአገራችን በፍጥነት በመሠራጨት ላይ የሚገኘውን ኤች አይ ቪ/ኤድስን ለመከላከልና ለመቆጣጠር ከሚያደርገው ጥረት በተጨማሪ የተለያዩ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ለጉዳዩ ትኩረት በመስጠት አበረታች እንቅስቃሴ በማድረግ ላይ ይገኛሉ። በመሆኑም በዚህ ዘርፍ የሚደረገውን ጥረትና ቅንጅታዊ አሠራር ከበፊቱ በተሻለ መልኩ አጠናክሮ ለመቀጠል እንዲቻል የሚከተሉትን ተግባራት ማከናወን ይገባል።

### ተግባራት

- በዘርፉ የፀረ-ኤድስ እንቅስቃሴዎችን ማቀድና ተግባራዊ ማድረግ፣
- በፀረ ኤድስ እንቅስቃሴ ዙሪያ ለተሰማሩ ክፍሎች የገንዘብ፣ የሙያ፣ እና-የማቴሪያል ድጋፍ ማድረግ ፣
- በክልሉ በኤች.አይ.ቪ/ኤድስ መከላከልና መቆጣጠር ስራ ለተሰማሩ አካላት በአገር ውስጥና በውጪ የሚደረጉ የልምድ ልውውጦችን ለማድረግ የሚያስችል ሁኔታዎችን ማመቻቸትና ዕገዛ ማድረግ፣
- በፀረ ኤድስ እንቅስቃሴ ዙሪያ ከክልልም ሆነ ከፌዴራል ኤች አይ ቪ/ኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ ሴክሬታሪያት እንዲሁም ከሌሎች



አካላት በሚገኝ የገንዘብ ድጋፍ የሚያደርጉትን እንቅስቃሴ ፕሮጀክቱ ተግባራዊ በሚሆንበት አካባቢ በየደረጃው ለሚገኙ የኤች አይ ቪ/ኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ ሴክሬታሪያት ጽ/ቤት ማሳወቅ፣
- በፀረ-ኤድስ እንቅስቃሴ ዙሪያ የሚቀረፁ ፕሮጀክት ፕሮፖዛሎች የህብረተሰቡን ፍላጎት መሠረት ያደረጉና የስራ ድግግሞሽን የማይፈጥሩ እንዲሆኑ ለማድረግ፣
- በአካባቢው በሚገኘው የኤች አይ ቪ/ኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ ጽ/ቤት በማስገምገም ለሚመለከተው ክፍል እንዲቀርብ ማድረግ፣
- ስምምነት ተፈፅሞባቸው ተግባራዊ በመሆን ላይ ያሉ እና የተጠናቀቁ ፕሮጀክቶች በሚመለከታቸው አካላት ተገቢው ክትትልና ግምገማ እንዲደረግባቸው ማስቻል፣
- የፀረ-ኤድስ ክበባትንና ማኅበራትን ማቋቋምና ማጠናከር፣
- በየደረጃው ለተቋቋሙ የፀረ ኤድስ ም/ቤቶች፣ ጽ/ቤቶችና ኮሚቴዎች አስፈላጊውን ዕገዛ ማድረግ።
- ከሚመለከታቸው የመንግስት አካላት ጋር በመቀናጀት የገቢ ማሰባሰቢያ ፕሮግራሞችን በማዘጋጀት ከቫይረሱ ጋር ለሚኖሩ ወገኖች፣ ለኤድስ ህሙማንና በኤድስ ምክንያት ወላጆቻቸውን ላጡ ልጆች እንክብካቤና ድጋፍ ማድረግ፣
- በዘርፉ የሚገኙ ሠራተኞችና ከስራው ጋር ግንኙነት ያላቸው የህብረተሰብ ክፍሎች በፈቃደኝነት ላይ የተመሠረተ የደም ምርመራ እንዲያደርጉ መቀስቀስና ማበረታታት፣
- በኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ዙሪያ የተለያዩ ስልጠናዎችንና የምክር አገልግሎት መስጠትና አፈፃፀሙን መከታተል፣

- የመረጃ፣ ትምህርትና ስርፀት /የባህሪ ለውጥ ስርፀት ( IEC/BCC ) ማቴሪያሎችን ከሚመለከተው አካል ጋር በመሆን ማዘጋጀትና አስገምግሞ እንዲሰራጩ ማድረግ፣
- በአባላዘር በሽታዎች መከላከል ላይ ከጤና ተቋማት ጋር በመተባበር ጉልህ አስተዋፅኦ ማበርከት፣
- ኤች.አይ.ቪ/ኤድስን በሚመለከት የሚወጡ ፖሊሲዎችን፣ መርሃ ግብሮችን፣ መመሪያዎችን፣ አዋጆችና ደንቦችን ለህብረተሰቡ ማስተዋወቅና የፖሊሲ ኃሳቦችን ማመንጨት፣
- በቂ የኮንዶም አቅርቦት እና ስርጭት እንዲኖር ማድረግ፣
- በክልሉ ለእድሜ ማራዘሚያነትና ቫይረሱ ከእናት ወደ ልጅ እንዳይተላለፍ ለማድረግ የሚያስችሉ መድሃኒቶች የሚገኙበትን ሁኔታ ማመቻቸት፣
- ከቫይረሱ ጋር የሚኖሩና የኤድስ ህሙማን እንዲሁም በኤድስ ምክንያት ወላጅ አልባ የሆኑ ልጆች በዕለት ከዕለት እንቅስቃሴአቸው ሰብአዊ መብቶቻቸው እንዳይጣሱና ነፃነቶቻቸውም እንዳይገሰሱ የበኩላቸውን ጥረት ማድረግ፣
- ከቫይረሱ ጋር የሚኖሩ፣ የኤድስ ህሙማን እና በኤድስ ምክንያት ወላጆቻቸውን ያጡ ልጆች ማህበር እንዲመሰርቱና ህብረተሰቡን ማስተማር እንዲችሉ ሁኔታዎችን ማመቻቸት፣ የራስ ማስቻያ ኘሮግራም ማካሄድና በገንዘብ መደገፍ፣
- የተሻለ የፀረ-ኤድስ እንቅስቃሴ ካላቸው ክፍሎች ጋር የልምድ ልውውጥ ማድረግ፣



- በክልሉ የኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ግንኙነት አውታር /Networking/ እንዲመሠረትና እንዲጠናከር ያላሰለሰ ጥረት ማድረግ፣
- በዘርፉ የኤች.አይ.ቪ/ኤድስን ስርጭት፣ ገፅታና የህብረተሰቡን የባህሪ ለውጥ በሚመለከት፣ የቅኝትና ጥናታዊ ስራ መስራት፣ውጤቱንም ማሳወቅ፣
- በዘርፉ በተደረገው የፀረ-ኤድስ እንቅስቃሴ የተገኘውን ለውጥ መገምገም፣ ስህተቶችን ማረም፣
- የፀረ-ኤድስ እንቅስቃሴ ሪፖርቶች ወቅታቸውን ጠብቀው ለሚመለከተው ክፍል እንዲቀርቡ ማድረግ፣

**ትውልድን ለማዳን**

**ኤች.አይ.ቪ/ኤድስን በጋራ እንከላከል!**

# 18. ህብረተሰብ አቀፍ ማህበራት / CBOs /

በክልሉ የተለያዩ ህብረተሰብ አቀፍ ማህበራት መኖራቸው ይታወቃል:: ምንም እንኳን የተለያየ አላማ ይዘው የተደራጁ ቢሆንም ማኅበራቱ የፈጠሩት አደረጃጀት አመቺ በመሆኑ በፀረ-ኤድስ እንቅስቃሴ ዙሪያ የማይናቁ በርካታ ተግባራትን ማከናወን ይችላሉ::

እንዲያውም እነዚህን ሀገር በቀል ማኅበራትን በቀናጀ መንገድ ኤች.አይ.ቪ/ኤድስን በመከላከልና በመቆጣጠር ዙሪያ ለማሳተፍ ካልተቻለ ጥረታችን ውጤታማ የመሆኑ ነገር አጠያያቂ እስከ መሆን እንደሚደርስ መገንዘብ ይኖርብናል:: ስለዚህ ህብረተሰቡ በአካባቢው ያቆማቸውና ያደራጃቸው እነዚህ ባህላዊ መዋቅሮች ኤች.አይ.ቪ/ኤድስን በመከላከልና በመቆጣጠር ዙሪያ የሚከተሉትን ተግባራት መፈፀም እንደሚችሉ ይታመናል::

## ተግባራት

- የፀረ-ኤድስ እንቅስቃሴዎችን ማቀድና ተግባራዊ ማድረግ፣
- በፀረ-ኤድስ እንቅስቃሴ ከተሰማሩ አካላት ጋር በመቀናጀት የገቢ ማሰባሰቢያ ኘሮግራሞችን በማዘጋጀት ከቫይረሱ ጋር ለሚኖሩ ወገኖች፣ ለኤድስ ህሙማንና፣ በኤድስ ምክንያት ወላጆቻቸውን ላጡ ልጆች እንክብካቤና ድጋፍ ማድረግ፣



- በዘርፉ የሚገኙ አባላትና ከዘርፉ ጋር ግንኙነት ያላቸው የህብረተሰብ ክፍሎች በፈቃደኝነት ላይ የተመሠረተ የደም ምርመራ እንዲያደርጉ መቀስቀስና ማበረታታት ፣
- ፀረ-ኤድስ ኘሮጀክቶችን በመቅረፅና ለሚመለከታቸው በማቅረብ ድጋፍ ማፈላለግና ተግባራዊ ማድረግ፣
- በኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ዙሪያ የተለያዩ ስልጠናዎችን መስጠትና ተግባራዊነቱን መከታተል፣
- ወጥነት ያላቸው የመረጃ፣ ትምህርትና ስርፀት/ የባህሪ ለውጥ ሥርፀት ( IEC/BCC ) ማቴሪያሎችን እንዲሁም ኮንዶሞችን ከሚመለከታቸው አካላት በማሰባሰብ ማሰራጨት፣
- ኤች.አይ.ቪ/ኤድስን በሚመለከት የሚወጡ ፖሊሲዎችን፣ መርሀ ግብሮችን፣ መመሪያዎችን፣ አዋጆችንና ደንቦችን ለአባላትና ለህብረተሰቡ ማስተዋወቅ፣
- በዘርፉ ፀረ-ኤድስ ኮሚቴዎችን ማቋቋምና ማጠናከር፤ የተሻለ የፀረ-ኤድስ እንቅስቃሴ ካላቸው ክፍሎች ጋር የልምድ ልውውጥ ማድረግ፣
- ከሚመለከታቸው አካላት ጋር የቅንጅት ስራ መስራት፣
- ለኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ስርጭት መባባስ ምክንያት የሆኑ ጎጂና ልማዳዊ ድርጊቶችን በመለየት እንዲወገዱ ህብረተሰቡን ማስተማር፣
- ከቫይረሱ ጋር የሚኖሩ ወገኖች፣ የኤድስ ህሙማን እና በኤድስ ምክንያት ወላጅ አልባ የሆኑ ልጆች ማህበር እንዲመሰርቱና ህብረተሰቡን እንዲያስተምሩ ማበረታታት፣

- ከቫይረሱ ጋር የሚኖሩና የኤድስ ህሙማን እንዲሁም በኤድስ ምክንያት ወላጅ አልባ የሆኑ ልጆች በዕለት ከዕለት እንቅስቃሴአቸው ሰብአዊ መብቶቻቸው እንዳይጣሱና ነፃነቶቻቸውም እንዳይገሰሱ ጥረት ማድረግ፣
- በዘርፉ በተደረገው የፀረ-ኤድስ እንቅስቃሴ የተገኘውን ለውጥ መገምገም፣
- የተከናወኑ የፀረ-ኤድስ ተግባራትን ለሚመለከተው አካል ሪፖርት ማድረግ፡፡

***ከልጆቻችንና ከህብረተሰቡ ጋር ስለኤች.አይ.ቪ/ኤድስ በግልጽ ለመወያየት የወላጆች ኃላፊነት ከፍተኛ ነው!***



# 19. የሃይማኖት ተቋማት

በክልላችን የተለያዩ የሃይማኖት ተቋማት እንደሚገኙ ይታወቃል፡፡ እነዚህም ተቋማት የየራሳቸው ባህሪና ልዩነት ቢኖራቸውም የመመካከር፣ የመቻቻል፣ የመፈቃቀር፣ የመተጋገዝና ባጭሩ ለራሳችን በጎ እንዲሆንልን እንደምንመኘው ሁሉ ለሌላውም በጎ ማሰብና ማድረግ እንዳለብን ያስተምራሉ፡፡ ይህ የሞራል ትምህርት ለኤች.አይ.ቪ ኤድስ መከላከልና መቆጣጠር ትልቅ አስተዋጽኦ አለው፡፡ እነዚህ የሃይማኖት ተቋሞች በዋናነት ጥንቃቄ በጎደለውና ፈር በለቀቀ ወሲባዊ ግንኙነት የሚተላለፈውን ኤች.አይ.ቪ/ኤድስን ለመግታትና የዕምነት ተከታዮቹን ደህንነት ለመጠበቅ ከፍተኛ ሚና ሊጫወቱ እንደሚችሉ የብዙዎች እምነት ነው፡፡

በመሆኑም በዚህ ዘርፍ የተሰማሩ የኃይማኖት ተቋማት ከዚህ የሚከተሉትን ተግባራት ማከናወን ይጠበቅባቸዋል፡፡

### ተግባራት

- በየደረጃው ባሉ የኃይማኖት ተቋማትና የእምነት መሪዎች አማካይነት ህብረተሰቡ ዕምነቱን በመጠበቅ እያንዳንዱ ራሱንና ቤተሰቡን ከኤድስ እንዲከላከል በዕቅድ የተደገፈ የተጠናከረ ትምህርትና ቅስቀሳ መስጠት፣
- ከቫይረሱ ጋር የሚኖሩ ወገኖች፣ የኤድስ ህሙማንና በኤድስ ምክንያት ወላጆቻቸውን ያጡ ልጆች በህብረተሰቡ እንዳይገለሉ ይልቁንም አስፈላጊውን እንክብካቤና ድጋፍ እንዲደረግላቸው ለህብረተሰቡ ያላሰለሰ ትምህርትና ቅስቀሳ ማድረግ፣

- የኤድስ ህሙማንን በመኖሪያ ቤታቸው በመገኘት መጎብኘት፣ ማስታመም፣ ማጽናናት አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ መንፈሳዊ የምክር አገልግሎት መስጠት፣
- የኃይማኖት ተቋማት መሪዎች ለበሽታው ልዩ ትኩረት በመስጠት ተቆርቋሪነትና ቁርጠኝነት በማሳየት እየተሸረሸረ ያለውን የግብረ ገብነት ትምህርት ማጠናከር፣
- በተመሳሳይ ሥራ ከተሰማሩ አካላት ጋር በመቀናጀት የገቢ ማሰባሰቢያ ኘሮግራሞችን በማዘጋጀት ከቫይረሱ ጋር ለሚኖሩ ወገኖች ለኤድስ ህሙማንና፣ በኤድስ ምክንያት ወላጆቻቸውን ላጡ ልጆች እንክበካቤና ድጋፍ ማድረግ፣
- ፀረ ኤድስ ኘሮጀክቶችን በመቅረጽና ለሚመለከታቸው በማቅረብ ድጋፍ ማፈላለግና ተግባራዊ ማድረግ፣
- በኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ዙሪያ የተለያዩ ስልጠናዎችን መስጠትና ተግባራዊነቱን መከታተል፣
- የመረጃ ትምህርትና ስርፀት/የባህሪ ለውጥ ሥርፀት ( IEC/BCC ) ማቴሪያሎችን በማዘጋጀት ወይም ከሚመለከታቸው በማሰባሰብ ማሰራጨት፣
- ኤች.አይ.ቪ/ኤድስን በሚመለከት የሚወጡ ፖሊሲዎችን፣ መርሃ ግብሮችን፣ መመሪያዎችን፣ አዋጆችና ደንቦችን ለህብረተሰቡ ማስተዋወቅ፣
- የተሻለ የፀረ-አድስ እንቅስቃሴ ካላቸው ክፍሎች ጋር የልምድ ልውውጥ ማድረግ፣
- ከሚመለከታቸው አካላት ጋር የቅንጅት ሥራ መስራት፣
- በዘርፉ በተደረገው የፀረ-ኤድስ እንቅስቃሴ የተገኘውን ለውጥ መገምገም፣



- የተከናወኑ ፀረ-ኤድስ ተግባራትን ለሚመለከተው አካል ሪፖርት ማድረግ፡

# እየኖርን ሌሎች እንዲኖሩ እናድርግ!

# ማስታወሻ

## *ከኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ጋር የሚኖሩትን እና በኤድስ ምክንያት ወላጅ አልባ የሆኑ ወገኖቻችንን እንንከባከብ ! እንደግፍ !*

- “እኔ እጠነቀቃለሁ እናንተስ ?”
- ኃላፊነት የሚሰማው አፍቃሪና ተፈቃሪ እንሁን !
- የኤች.አይ.ቪ ቫይረስ በደማቸው ውስጥ ላለባቸው ሰዎች ፍቅርና እንክብካቤ እንስጣቸው !
- በኤች.አይ.ቪ/ኤድስ የተያዘውን ሰው በማየት ብቻ መለየት አይቻልም !
- ኤድስን ማዳን ባይቻልም መከላከል ይቻላል !
- ለህይወታችን ዋጋ እንስጥ !



# የአብክመ ኤች.አይ.ቪ/ኤድስ መከ/መቆ/ ሴክሬታሪያት

## <u>ራዕይና የተልዕኮ መግለጫ</u>

### <u>ራዕይ / Vision</u>

በአማራ ብሔራዊ ክልል የኤች አይ ቪ/ኤድስ በሽታ የሚያስከትለው ሰብዓዊ እልቂት፣ ኢኮኖሚያዊ ድቀት፣ ማህበራዊ ቀውስ እና የሥነ ልቦና ጉዳት ተወግዶ ማየት፣

### <u>የተልዕኮ መግለጫ / Mission Statement</u>

የኤች አይ ቪ/ኤድስ ቫይረስ በክልሉ እንዳይስፋፋ ዘላቂነት ያለው ኅብረተሰብ አቀፍ፣ የመከላከልና የመቆጣጠር እንቅስቃሴዎችን በተቀናጀና ውጤታማ በሆነ መንገድ ለማካሄድ እንዲቻል የመንግስት መ/ቤቶች፣ የሃይማኖት ድርጅቶች፣ የኅብረተሰብ አቀፍ ተቋማት /የወጣቶች ፀረ-ኤድስ ክበባትና ማኅበራት፣ እድሮች፣ የሴቶችና ወጣቶች ማኅበራት/ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችና ግለሠቦች የሚያደርጉትን ጥረት በመደገፍና በማስተባበር ከቫይረሱ ጋር የሚኖሩ ሰዎችና በቫይረሱ ምክንያት ቤተሰቦቻቸውን ያጡ ሕፃናት ቀጣይነት ያለውና ራስን የሚያስችል ድጋፍና እንክብካቤ የሚያገኙበትን ሁኔታ ለማመቻቸት፣ የአካባቢን ሀብት በዋነኛነት መሠረት የሚያደርግ ከተለያዩ ለጋሾች ጋር ግንኙነት በመፍጠር ድጋፍ ማፈላለግና በአግባቡ ጥቅም ላይ ማዋል፣

## የአብክመ ኤች.አይ.ቪ/ኤድስ መከ/መቆ/ ሴክሬታሪያት

## <u>የአሠራር መርሆዎችና እሴቶች</u> /Values /

1. በትልቁ እናስባለን፣ በትንሹ አሁኑኑ እንጀምራለን !
2. ከቫይረሱ ጋር የሚኖሩ ወገኖችና ወላጅ አልባ ሕፃናትን ሰብአዊ መብቶቻቸውን እናከብራለን ! አድልዎና መገለል አናደርግም !
3. ሥራችንን ለማከናወን መደበኛ የሥራ ሰዓት አይገድበንም !
4. ከአጋሮቻችን ጋር በታማኝነት፣ በእኩልነትና፣ በፍትሃዊነት እንሰራለን !
5. በትምህርትም ይሁን በልምድ ያገኘነውን እውቀት ሥራችንን ለመፈፀም ተገቢ በሆነ መንገድ ሁሉ በተግባር ላይ እናውላለን !
6. የመ/ቤታችንን ቁሳዊና ሰብአዊ ሃብት በአግባቡ እንጠቀማለን !
7. ከተለያዩ ምንጮች የምናገኘውን ቁሳዊና የገንዘብ ሀብት በውጤታማ ሥራ ላይ እናውላለን!

የአብክመ የኤች.አይ.ቪ/ኤድስ መከ/መቆ/ ሴክሬታሪያት